# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 115 ታኅሣሥ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “የኢትዮጵያ የባሕር በር ፍላጎት አብሮ የመበልጸግ መርሕን የተከተለ እንጂ የማንንም ሉዓላዊነት የሚነካ አይደለም”

- አየለ በክሪ (ዶ/ር) የታሪክ ምሑር

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- በባሕር በር ጉዳይ የኢትዮጵያ ፍላጎት በስምምነት ላይ በመመስረት አብረን እንበልጽግ የሚል እንጂ የማንንም ሉዓላዊነት የሚነካ አይደለም ሲሉ የታሪክ ምሑሩ አየለ በክሪ (ዶ/ር) ገለጹ።

የታሪክ ምሑሩ አየለ በክሪ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ከሶማሌ ላንድ ጋር መፈራረሟን አስመልክቶ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ኢትዮጵያ ከጥንታዊው የአዱሊስ ዘመን እስከ መካከለኛው ዘመን በታሪክ ለረጅም ጊዜ የወደብ ባለቤት ሆና የቆየች ሀገር መሆኗን ጠቅሰዋል።

በታሪክ ኢትዮጵያ ትጠቀም የነበረው ወደብ ምጽዋና አሰብ ብቻ አልነበረም የሚሉት ዶክተር አየለ፤ በተለይ በእነ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ፣ አጼ ይስሐቅና አጼ ልብነድንግል ጊዜ ትጠቀም የነበረው “ዘይላ” የሚባለውን ወደብ ነበር ብለዋል። በዚህ ስፍራም አማርኛና ዓረብኛ ቋንቋ ይነገር እንደነበር አውስተዋል።

አሁን የተጀመረው የባሕር በር ባለቤት የመሆን እንቅስቃሴ ተገቢ መሆኑን በማንሳት፤ የሀገሪቷ ፍላጎት ሌሎች ላይ ጫና መፍጠርና ሉዓላዊነትን መንካት ሳይሆን ስምምነት ላይ የተመሠረተ የአብሮ ማደግና መበልጸግ

“የኢትዮጵያ የባሕር... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


ፎቶ፡ ገበዘ ገብሬ






### ስፖርት አብሮነትን በማጠናከር ረገድ ያለውን ሚና በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል

ገጽ 6

## በባሕር በር ጉዳይ ሕዝቡ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲያደርግ የማነቃቃት ሥራ ይሠራል

### - የባሕር በር ስምምነቱን ተከትሎ በተለያዩ ከተሞች የድጋፍ ሰልፍ ተካሂዷል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በባሕር በር ጉዳይ ላይ በምትሠራቸው ሥራዎች ሕዝቡ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲያደርግ የማነቃቃት ሥራ እንሠራለን ሲሉ የተለያዩ ከተሞች መንግሥት ኮሙኒዩኬሽን ኃላፊዎች ገለጹ። የኢትዮጵያ እና የሶማሌ ላንድን የወደብ ስምምነት ተከትሎ በተለያዩ ከተሞች የደስታ መግለጫ የድጋፍ ሰልፍ ተካሂዷል።

የድሬዳዋ ከተማ መንግሥት ኮሙኒዩኬሽን ቢሮ ኃላፊ ብሩክ ፈለቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ላለፉት 30 ዓመታት ያለ ባሕር በር በመቆየቷ በምጣኔ ሀብታዊ እድገቷ ላይ አሉታዊ ጫና አሳድሯል።

ሀገሪቱ በባሕር በር ዙሪያ በምትሠራው ሥራ ሕዝቡ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የኪነጥበብ ሥራዎችንና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የማነቃቃት ሥራ ይሠራል ብለዋል።

ስምምነት ላይ የተደረሰውን ወደብ የማልማቱ ሂደት

በባሕር በር ጉዳይ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

## በኢትዮጵያና ሶማሌ ላንድ መካከል የተፈረመው ስምምነት ማንንም የማይጎዳና ሰፊ የትብብር አድማሶችን ያካተተ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያና ሶማሌ ላንድ መካከል የተፈረመው ሁሉን አቀፍ የትብብርና አጋርነት የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ማንንም አካል የማይጎዳና

በኢትዮጵያና... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








# ለበዓላቱ ከዘጠኝ ሚሊዮን ሊትር በላይ ዘይት ለኅብረተሰቡ ይቀርባል

ታደሠ ብናልፈው



አዲስ አበባ፡- ለገናና ለጥምቀት በዓላት ከዘጠኝ ሚሊዮን ሊትር በላይ ዘይት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር የሀገር ውስጥ ንግድና ሸማቶች ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ መስከረም ባሕሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለገናና ለጥምቀት በዓላት ዘጠኝ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሊትር ዘይት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው።

በዘይት፣ በስኳር፤ በግብርና በእንስሳት ተዋፅዖ ምርቶች ላይ የዋጋ ንረትን ለማርገብ የተለያዩ ሥራዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ መስከረም፤ የዘይት አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰትና የዋጋ ንረቱንም ለማርገብ በገናና በጥምቀት በዓላት ዘጠኝ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሊትር ዘይትና ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ለማኅበረሰቡ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

በሀገሪቱ ያለውን የስኳር ክምችት እጥረት ለመፍታት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ ያሉት ወይዘሮ መስከረም የክምችት እጥረቱን ለመፍታት ባለፉት ስድስት ወራት 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል ስኳርና 8 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሊትር ዘይት ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እየተደረገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ባለፈው ኅዳር ወር ብቻ ከቀረጥ ነፃ በሆነ መንገድ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሊትር ዘይትና 450 ሺህ ኩንታል ስኳር ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ሥራ ተሠርቷል፤ የገባውም ምርት ሸማችንና አምራችን በቀጥታ በሚያገናኝ መንገድ ማለትም በ856 የቅዳሜና የእሁድ ገበያዎች፤ በችርቻሮ ሱቆች፣ በኅብረት ሥራ ኤጀንሲዎችና በተለያዩ መንገዶች ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እየተደረገ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በበዓላት ወቅት የሚታይ ፍላጎትንና አቅርቦትን ለማጣጣም በመንግሥት በኩል በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ መስከረም፤ እየተሠራ ባለው ሥራም የዘይት፤ የስኳር፤ የግብር ምርቶችና ተዋፅዖዎች ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እየሆኑ ነው ብለዋል።

በተለይ የዘይትና የስኳር ምርቶች ላይ የአቅርቦት መጠን እየቀነሰ የመጣበት ሁኔታ ነበር ያሉት ሥራ አስፈፃሚዋ፤ የአቅርቦት ችግሩን ለመፍታት ከውጪ ያለቀረጥ በነፃ እንዲገቡ በማድረግ ችግሩን የመፍታት ሥራ ተሠርቷል ሲሉ አብራርተዋል።

ወይዘሮ መስከረም አክለውም፤ በዓላትን ምክንያት በማድረግ በግብርና ምርቶችና በእንስሳት ተዋፅዖ ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ምርቶች ለማኅበረሰቡ በኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት ለማቅረብ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እየተሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ሥራ አስፈፃሚዋ፣ በበዓሉ ወቅት የሚታዩ አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪዎችንና ሕገ ወጥ ንግድን ለመቆጣጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተሠራ ነው ሲሉ አመላክተዋል።



ኢንጅነር አይሻ መሐመድ

## የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮች ኤክስፖ ሊካሄድ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ከጥር 17 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም የሚቆይ የአርብቶ አደሮች ኤክስፖ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ሊካሄድ መሆኑን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሚኒስትር ኢንጅነር አይሻ መሐመድ ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፣ ኤክስፖው የሚካሄደው ‹‹አርብቶ አደርነት፣ የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረ ቀለም›› በሚል መሪ ቃል ነው።

ሃገራችን ኢትዮጵያ እምቅ የመልማት አቅም ያላት መሆኗን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፣ የአርብቶ አደርና ቆላማ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ደግሞ ለልማት ምቹ የሆኑ ሰፋፊ መሬቶች፣ ማዕድናትና የእንስሳት ሀብት ባለቤት መሆናቸውን ገልፀዋል።


ከጥር17-24 ቀን 2016 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ የሚካሄደው የአርብቶ አደሮች ኤክስፖም ይህንን በሚያጎላ መልኩ እንደሚካሄድ አብራርተዋል።

በዚሁ ኤክስፖ ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የተወከሉ አርብቶ አደሮችና በዘርፉ ላይ ምርምርና ጥናት የሚያደርጉ ተቋማትና ባለሙያዎች እንደሚገኙ ያመለከቱት ሚኒስትሯ የአርብቶአደር አካባቢዎች ስለሚሠሯቸው ሥራዎች ራሳቸውን የሚያስተዋውቁበት፣ የእርስ በርስ ልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት፣ ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት አርብቶ አደሮችም ጋር ልምድ በመለዋወጥ የዘርፉን ሃገራዊ ፋይዳ የምናሳይበት ይሆናል ሲሉ አብራርተዋል።

የአርብቶ አደሮች ቀን ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲከበር የቆየ በዓል ሲሆን ዘንድሮ ግን ከፍ ባለና ቀጣናዊ ትስስርን በሚፈጥር መልኩ ከምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት ድርጅት (IGAD) ጋር በመተባበር የሚካሄድ መሆኑንም ተመልክቷል።

## የገና እና የጥምቀት በዓላት በክልሉ የተቀዛቀዘውን የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃት ያስችላሉ

ማሕሌት ብዙነህ



አዲስ አበባ፡- የገና እና ጥምቀት በዓላት በክልሉ የተቀዛቀዘውን የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃት የሚያስችሉ መሆኑን የአማራ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አበበ እምቢአለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የገና እና ጥምቀት በዓላት በድምቀት ከሚከበርባቸው አካባቢዎች አማራ ክልል በቀደምትነት ይጠቀሳል። እነዚህ በዓላት በክልሉ ተቀዛቅዞ የቆየውን የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃት የሚያችሉ በመሆናቸው በትኩረት እየተሠራ ነው።

በክልሉ በተፈጠረው የሰላም እጦት ምክንያት የከተማው ምጣኔ ሀብት ከፍተኛ መቀዛቀዝ አሳይቷል ያሉት አቶ አበበ፤ ሁለቱን በዓላት በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ክልሉን ብሎም ሀገሪቱ ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ በደመቀ ሁኔታ ለማክበርም የዝግጅት ሥራዎችን እየተሠሩ ነው ብለዋል።

ዘንድሮ በታኅሣሥ 28 የሚከበረውን የገና በዓል በላሊበላ ከተማ ለማክበር የከተማው አስተዳደር ኮሚቴ ከማቋቋም ጀምሮ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደርና የቱሪዝም ቢሮ ከክልሉ ጋር በመሆን ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

በተመሳሳይም በደመቀ መልኩ በጎንደር የሚከበረው የጥምቀት በዓል እንደክልል ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ባለፈው ዓመት በሁለቱ በዓላት ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በእያንዳንዳቸው ላይ የተገኘ መሆኑን አቶ አበበ አስታውሰዋል። በዚህ ዓመትም ተመሳሳይ መልኩ በደመቀ መልኩ ለማክበር እና ቀጣይነት እንዲኖረውን ይሠራል ብለዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የገና እና ጥምቀትን በዓላትን ታሳቢ በማድረግ በክብረ በዓሉ ለመታደም የሚመጡ ጎብኚዎች ከባሕርዳር ላሊበላ እና ከጎንደር ላሊበላ ለመንቀሳቀስ በቀጥታ የአየር ትራንስፖርት መፍቀዱን ገልጸዋል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ፓኬጁን ቁጥርን እንዲጨምር ለማድረግ የክልሉና ፌዴራል ቱሪዝም ቢሮ እየሠራ መሆኑን አቶ አበበ አስታውቀዋል።

የእነዚህ በዓላት ብሎም የሠላም ባለቤቱ ሕዝብ በመሆኑ በክልሉ የተፈጠረውን አንጻራዊ ሰላም በማስቀጠል እንግዶች በዓላቱን ከማክበር ባለፈ የሚጎበኙ ቦታዎችን እንዲጎበኙ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና ማስቀጠል ይገባል ነው ያሉት።

በክልሉ የሚገኙ ሆቴሎች፣ ትራንስፖርት፣ አስጎብኚ ማኅበራትና መሰል አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በጋራ እየተዘጋጁ መሆኑን አቶ አበበ ገልጸዋል።

አቶ አበበ እንደገለጹት፤ ቀደም ሲል በተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ እና የሠላም ችግር ምክንያት በክልሉ የውጭ ቱሪስቶች ቁጥር መቀነስ ያሣያል። ለዚህም ቢሮው የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት በማድረግ ያለውን የጎብኚዎች እጥረት ለማካካስ እየሠራ ነው።

በክልሉ ያሉትን ሰፊ የባሕልና የቱሪዝም መዳረሻዎች ምቹ በማድረግ እንዲሁም አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በመደገፍ ዘርፉን በድጋሚ የማንሰራራትና የሚገኘውን ተጠቃሚነት ማሳደግ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ ቢሮው ከመንግሥት እና በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት ጋር በመሆን በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

አቶ አበበ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላቱን ለማክበር የሚመጡ እንግዶች በክልሉ በነፃነት መንቀሳቀስና መጎብኘት የሚቻል መሆኑን ታሳቢ በማድረግ እንዲጎበኙ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል ።

# ማኅበራት ከገዢዎች ጋር ትስስር መፍጠራቸው ኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶችን እንዲሸምት አስችሏል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በገና በዓል ኅብረተሰቡ በተጋነነ የገበያ ዋጋ እንዳይጎዳ በፌዴራል ደረጃ 27 የኅብረት ሥራዎች ከገዢዎች ጋር ማስተሳሰሩን ኅብረት ሥራዎች ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽነር ጌታቸው መለሠ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ ሰው ተኮር ከመሆናቸው አንጻር ኅብረተሰቡን ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ምርት እያቀረቡ ይገኛሉ። ለገና በዓልም ለማኅበረሰቡ በተመጣጠነ ዋጋ ምርት እያቀረቡ ነው። በዓላትን አስታኮ ኅብረተሰቡ በተጋነነ የገበያ ዋጋ እንዳይጎዳ በፌዴራል ደረጃ 27 የኅብረት ሥራዎችን ከሦስት ገዢዎች ጋር በማስተሳሰር ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል።

የኅብረት ሥራ ማህበራት በተጋነነ ትርፍ ላይ የተመሠረቱ ስላልሆኑ ከሌላው በተለየ መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚ ማኅበረሰብ ማቅረብ ማኅበራዊ ኃላፊነት እንዳለባቸው ነው ኮሚሽነሩ ገልጸዋል። ማኅበራቱ እንደ አንድ የገበያ ተዋናይ በተለይ በበዓላት ወቅት ዋጋን በማረጋጋት ሂደት ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከቱ እንዳለም ጠቅሰዋል።

ዋጋን ማረጋጋት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባር



ብቻ አይደለም ያሉት ኮሚሽነሩ፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በሀገር ውስጥ ግብይት ድርሻቸው ከዘጠኝ እስከ 18 በመቶ መሆኑና ሌላኛው ከ80 በመቶ የሚደርሰው ግብይት ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ውጪ እንዳሆነም ገልጸዋል። ማኅበራቱ ባላቸው የገበያ ድርሻ ግን እንደ ሀገር ትልቅ አዎንታዊ ሚና እንዳላቸው አስታውቀዋል።

አጠቃላይ ያለውን የገበያ ሁኔታ ለማረጋጋት ማኅበራቱ የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ እየተሠራ እንደሆነ በመጥቀስ፤ አሁን ባላቸው አቅም በተመጣጠነ ዋጋ ምርት እንዲያቀርቡ እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በዚህም የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ከገዢዎች ጋር የማስተሳሰር ሥራ እየተከናወነ እንዳለ ተናግረዋል። በተለይ ለገና በዓል አገልግሎት በሰብልም ሆነ በእንስሳት ግብይት የማስተሳሰር ሥራ መሠራቱን ጠቅሰዋል።

እንደ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ የመሳሰሉ የሰብል ምርቶች፤ እንዲሁም ሽንኩርትን ጨምሮ ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ለዓመት በዓሉ እንዲደርሱ የኅብረት ሥራ ማኅበራትንና ገዢዎችን የማስተሳሰር ሥራ መሠራቱን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፤ በአዲስ አበባም ሆነ በክልሎች ነዋሪው በገበያ ዋጋ እንዳይጎዳ በተመጣጠነ ዋጋ ምርት እንዲያገኝ ለማድረግ ከሁሉም ክልሎች የተወጣጡ 27 የሚሆኑ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተለይተው ከአዲስ አበባ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ሥራ ኮርፖሬሽንና፣ ከኢንዱስትሪ ግብዓት አቅራቢ ድርጅት ጋር የማናኘት ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል።

የሁሉም ክልል ባለድርሻ አካላት አመራሮች በተገኙበት የገበያ ትስስሩ መፈጸሙንም ገልጸዋል።

የገበያ ትስስርን ለማስፋት በየካቲት ወር ላይ ኮሚሽኑ የኤግዚቢሽንና ባዛር ሁነት ማዘጋጀቱንም ጠቁመዋል።



# “በከተማዋ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያ በብልጽግና ጎዳና ላይ መሆኗን ያሳያሉ ”

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የተገነቡና እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያ በብልጽግና ጎዳና ላይ መሆኗን የሚያሳዩ መሆናቸውን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየምን ለአዲስ አበባ ከተማ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባላት ትናንት አስጎብኝተዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባ በርካታ የልማት ሥራዎች እየተከናወነ ነው። የሚሠሩት የልማት ሥራዎች ሁሉንም ማኅበረሰብ የሚያማክሉ መሆናቸው ልዩ ያደርጋቸዋል። የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየም፣ የምገባ ማዕከላት ግንባታ፣ እየተገነባ ያለው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ስታዲየም፣ ረጅም ድልድዮች እና አዳዲስ መንገዶች፣ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ሌሎች ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያ በብልጽግና ጎዳና ላይ መሆኗን ያስረዳሉ።

እነዚህ እየተሠሩ ያሉ ፕሮጀክቶች የአረንጓዴ አሻራ ልማትን አካተዋል። ለብዙ ዜጎችም የሥራ እድል ፈጥረዋል። አርሶ አደሮችንም ተጠቃሚ አድርገዋል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በቀጣይም የሕዝቡን የኑሮ ጫና፣ የአዲስ አበባን ገጽታንና መሠረተ ልማቶች የሚያሻሽሉ ሥራዎች ለመሥራት መታቀዳቸውን ገልጸዋል።

የተጠናቀቁት፣ እየተገነቡ ያሉትና በአሥር ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅድ መሠረት የሚገነቡት ፕሮጀክቶች ለቱሪዝም መስሕብነት የሚያገለግሉና የከተማዋን ገቢ የሚያሳድጉ መሆናቸውን ገልጸው፤ ከዚህም ባለፈ ማኅበራዊ መስተጋብርን የሚያጠናክሩ እና የኑሮ ጫናን የሚያቃልሉ ፕሮጀክቶች ናቸው ብለዋል ።

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለፃ፤ በከተማዋ እየተሠሩ ያሉት የልማት ሥራዎች አመራሩን፣ የልማት ኃይሎችን፣ ባለሃብቶችንና ማኅበረሰቡን በማስተባበር የተሠሩ ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም የከተማዋን ገጽታ ለመቀየር በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል። ከነዚህም ውስጥ አንድነት ፓርክ፣ እንጦጦ ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ ቁጥር አንድና ሁለት ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህም የውጭ ሀገራት መሪዎችን ስንቀበል በኩራት እንዲሆን እድል ፈጥረዋል ብለዋል።

ከሁሉ በላይ በተገነቡት ቦታዎች የከተማዋ ሕፃናት ሲቦርቁ፣ ሲጫወቱና ሲደሰቱ ማየት ትልቅ ደስታን ይፈጥራል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ይህም ተጨማሪ ሜጋ ፕሮጀክቶችን፣ መዝናኛ ፓርኮችን፣ የምገባ ማዕከላትን፣ አረንጓዴ አካባቢን እና ሌሎች ሰው ተኮር ሥራዎችን ለመገንባት እንዳነሳሳቸው ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ የሚገኙ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ከጎበኟቸው ፕሮጀክቶች መካከል በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በ60/90 ቀናት የግል ባለሀብቶችንና ኅብረተሰቡን በማሳተፍ የተሠሩ ሰፋፊ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል ይገኙበታል።

የለሚ ኩራ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች የክፍለ ከተማውን ገፅታ ከመቀየር ባለፈ በሺዎች ለሚቆጠሩ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠራቸው በጉብኝቱ ላይ ተገልጿል።

አምራቹንና ሸማቹን በቀጥታ በማገናኘት፣ የገበያ ሰንሰለቶችን በማሳጠር የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ከተገነቡ ግዙፍ የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከላት አንዱ የሆነውን የለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከልም የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ጎብኝተውታል።

ለበርካታ እናቶች ዘላቂ የገቢ ምንጭ የሆነውና ለግለሰቦች እና ለተቋማት ጥራቱን የጠበቀ እንጀራ በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ የሚገኘው ለሚ እንጀራ ፋብሪካ እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የተገነቡ የመኖሪያ ቤቶች፣ የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት እና ሌሎችም ሰው ተኮር የልማት ፕሮጀክቶች የጉብኝቱ አካል ናቸው።



# በገናና ጥምቀት በዓላት የአቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት ዝግጅት ተደርጓል

## - ለበዓላቱ የምርት ግብዓቶችን የሚያቀርቡ ባዛሮች ተከፍተዋል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በገናና ጥምቀት በዓላት የአቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት በቂ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታወቀ። በአምስት የተመረጡ ቦታዎች ሳምንቱን ሙሉ የተለያዩ የምርት ግብዓቶችን የሚያቀርቡ ባዛሮች መከፈታቸውን ገልጿል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ሰውነት አየለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የገና እና ጥምቀት በዓላት በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ የሚከበሩ በመሆናቸው ግብዓቶች በከፍተኛ ሁኔታ ያስፈልጋሉ። ቢሮው በበዓላቱ የምርት እጥረት እንዳይከሰትና የዋጋ ግሽበት እንዳይኖር ግብረ ኃይል በማቋቋም እየሠራ ነው ።

ኅብረተሰቡ ለበዓላቱ የሚጠቀማቸውን ግብዓቶች በስፋት ለማቅረብ በከተማዋ ዋና ዋና ቦታዎች ላይ ባዛሮችን ማዘጋጀቱንም ጠቁመዋል።

አቶ ሰውነት እንዳሉት፤ በባዛሮቹ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ ለበዓል ተፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ይቀርባሉ። የበዓል ባዛሮቹ ሳር ቤት፣ መገናኛ፣ ስድስት ኪሎ እና መሰል ሸማች ይበዛል ተብለው በሚታሰቡ ቦታዎች ላይ ተከፍተዋል።

በባዛሮቹ ከተለያዩ አካባቢዎች የተውጣጡ አምራች እና አቅራቢዎች እንዲሳተፉ ያደረገ መሆኑን አቶ ሰውነት አስገንዝበዋል።

በተለይም ምርት በቀጥታ ከሚያመርቱ አርሶ አደሮች እና አምራች ማኅበራት ጋር ትስስር በመፍጠር በቂ አቅርቦት በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብበትን እድል መፍጠር ተችሏል ብለዋል።

በተጨማሪም የሰንበት ገበያዎች የአገልግሎት ቀን እንዲሠፋ የሚደረግ መሆኑን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በከተማዋ ባሉ 172 የሰንበት ገበያዎች ከሰኞ እስከ ሰኞ አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ ይህም በዓላቱን ምክንያት በማድረግ የተጋነነ የዋጋ ግሽበት እንዳይፈጠር ይረዳል ብለዋል።

የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ ላይ ክትትሎች እንደሚደረጉ ጠቁመዋል።

የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይም ጠንካራ ቁጥጥር እና ክትትል እየተደረገ ነው ብለዋል።

በዓላቱን ምክንያት አድርገው የተለለያዩ ሕገወጥ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ አካላት ላይ በተለይም ምርቶችን የሚደብቁ ነጋዴዎችን ላይ ርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ሲሉም ገልጸዋል።

የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ነጋዴዎች በቅዳሜ እና እሁድ ገበያ ከመደበኛው የገበያ ዋጋ ከ15 እስከ 20 በመቶ ቀንሰው እንዲሸጡ ስምምነት ላይ መደረሱን የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ሰውነት አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አብሮነታችን ለጋራ ሠላምና ብልጽግናችን መሠረት ነው!

አብሮነት መተዋወቅን፣ መቀራረብን፣ መተሳሰብና መደጋገፍን፣ በጥቅሉም እህትማማችነትንና ወንድማማችነትን የሚፈጥር የሰውነት እሴትና ባሕሪ ነው:: አብሮነት በዚህ መልኩ ማኅበራዊ መሠረት የሚያጎለብት ብቻ ሳይሆን፤ በወንድማማቾች መካከል መተዋወቅና መተሳሰብን በማጽናት ውስጥ፣ በብዝኃነት የሚገለጥ አንድነትን የሚጎለብት፤ ተግባብቶ በመተባበር ውስጥ የሚገለጥ ኃያልነትን የሚገነባ ታላቅ ዓውድ ነው::

አብሮነታቸው የበረታ ሕዝቦች እንደ ሕዝብ ጠንካራ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ብሎም ሥነልቡናዊ ከፍታን ተጎናጽፈዋል:: በሕዝቦች በኅብር የደመቀ መተባበር፤ በአብሮነት የጸና አንድነት ላይ ተመስርተው የተገነቡ ሀገራትም ሁለንተናዊ ብልጽግናቸውን፣ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነታቸውን አጽንተዋል:: በአንጻሩ ከዚህ በተቃራኒው የተጓዙ ሕዝቦች እና ሀገራት በድህነት፣ በኋላ ቀርነት፣ በመከፋፈልና ጦርነት ውስጥ ሲዳከሩ፤ እንደ ሀገር ፈርሰው፣ እንደ ሕዝብም ተበትነው ተገልጠዋል::

ዛሬ ላይ በልጽገውና የኃያልነት መንበርን ተቆናጥጠው የሚታዩ ሀገራት በሕዝቦቻቸው አብሮነት ላይ ተመሥርተው የተገነቡ ናቸው:: እነዚህ ሀገራት ጠንካራ ማኅበራዊ መሠረትን የገነቡ ሕዝቦች የእውቀት፣ የባሕልና እሴት ፍሬዎች እንደመሆናቸው ማንም ሰው ደርሶ ሊንጣቸው፣ ሊንዳቸው አልያም ሊያፈርሳቸው አይችልም:: ይልቁንም የትናንት የሕዝቦች አብሮነት ማዕከልነታቸው ለሌሎች በአርዓያነቱ እየተገለጠ የሚሄድ ነው::

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያንም በዚህ ረገድ ከትናንት እስከ ዛሬ የዘለቀው ታሪክና እሴታቸው በዚሁ ልክ የሚገለጽ ነው:: ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን አብሮነታቸው ታላቅ ሀገርን ፈጥሮላቸዋል፤ አብሮነታቸው ታላቅ የታሪክ ድልና ገድልን አስገኝቶላቸዋል፤ አብሮነታቸው ሉዓላዊነታቸውን እንዲያስጠብቁ፣ ባሕልና እሴታቸውን ከፍ አድርገው ሳይበረዝ አጽንተው እንዲይዙ አቅም ፈጥሮላቸዋል::

በባሕልና እሴት ከፍታቸው፤ በታሪክ ከታብ ገናነነታቸው፤ በነፃነትና በድል መንገዳቸው፤ በብዝኃነት ኅብር ድምቀታቸው ምክንያት የሆነው ይሄ አብሮነታቸው ታዲያ፤ ከትናንት እስከ ዛሬ በምቾት ላይ ምቾት ተላብሶ ያለ እንከን የዘለቀ አይደለም:: ይልቁንም ሲፈተን እና በፈተና ውስጥ የበለጠ እየጸናና እየጠበቀ በሄደ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትና ወንድማማችነት ላይ ሊመሠረት የቻለ እንጂ::

ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያዊነት የወል መገለጫቸው ላይ ተቆናጥጠው ረዥሙን ጉዞ ድካም ተቋቁመው፤ የረዥሙን ታሪክ ስንክሳር ተሻግረው፤ የረዥሙን ጉዞ ውጣ ውረድ አልፈው እንደ ቀደመው ሁሉ በአብሮነት ጸንተው መገኘታቸው:: ለዚህም ነው ኢትዮጵያን በዘመን ጅረት ውስጥ ነፃነትና ሉዓላዊነቷን በገናና የታሪክ ድርሳን ላይ ተከትቦ እንዲዘልቅ ማድረጋቸው::

የኢትዮጵያውያን አብሮነት መገለጫው ታዲያ አንድ ፈርጅ ብቻ አይደለም:: ይልቁንም እንደ ጊዜና ሁኔታው እየተቃኘ የሚታይ፤ ሊንደው ለሚሻ ማናቸውም የክፋት ኃይል ልፋቱን ከንቱ በሚያደርግ መስተጋብር የሚገለጥ ነው:: ምክንያቱም የኢትዮጵያውያን አብሮነት በባሕል ውስጥ ጎልቶ የሚታይ የተዋረሰ ባሕላዊ እሴትን ፈጥሯል:: የኢትዮጵያውያን አብሮነት ከፍ ባለ ማኅበራዊ ጉድኝት ውስጥ የሚከሰት የኢትዮጵያውያንን በደስታና በኃዘን የመተጋገዝ ሰብዓዊ ልዕልናን ገንብቷል::

የኢትዮጵያውያን አብሮነት በውስጥም በባንዳነት የሚነሳን፤ ከውጪም በጠላትነት የሚነሳን ማናቸውም ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ኃይል አንገት በሚያስደፋ የጀግንነት መሠረትን የገነባ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን አጽንቷል:: የኢትዮጵያውያን አብሮነት በየትኛውም ዓውድ ላይ ከፍ ብሎ የመገለጥን፤ የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ልዕልና ማስጠበቅን፤ ለችግር ያለመንበርከክና ለሁለንተናዊ ብልጽግና በጋራ መሰለፍን በዓለም አደባባይ መግለጥ ችሏል::

ይሄ የኢትዮጵያውያን የአብሮነት ገጽ የፈጠረው ሁሉን አቀፍ መገለጫ ታዲያ በትናንት ታሪክ ብቻ የሚተረክ አይደለም:: ይልቁንም ዛሬም በሚደንቅ ሁኔታ ኢትዮጵያን ወደ ከፍታዋ ለማድረስ፤ ኢትዮጵያውያንንም ወደ ክብር ቦታቸው ለመመለስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ እየታየ ያለ ሐቅ ነው:: የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ የተጀመረው ጉዞ እያሳየ ያለው ውጤት ደግሞ የዚህ እውነት ማጽኛ ዓውድ ነው::

ይሄ በትናንት ሁነት እና በዛሬ ኑረት ውስጥ የሚገለጠው የኢትዮጵያውያን አንድነት ታዲያ፤ ለነገው ትውልድ መሠረትን አኑሮ የመገለጥ ከፍ ያለ ግዴታ በዛሬው ባለ ሀገር ላይ የታለ መሆኑን መገንዘብ የተገባ ነው:: ምክንያቱም የትናንቶቹ ከችግሮቻቸው ልቀውና በአብሮነታቸው ዘልቀው ዛሬን ፈጥረዋል:: እናም የዛሬዎቹ የቀደምቶቻቸውን አደራ ጠብቀውና አልቀው ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል::

ይሄን የሚያደርጉት ታዲያ ከትናንቱ የአብሮነት ፈተናዎች መሻገሪያ አቅም ፈጥረው፤ ከመልካም ሁነቶቹ ተምረውና አዳዲስ እሴቶችን ገንብተው ሊሆን ይገባል:: በዚህ መልኩ የሚገነቡት አንድነት ደግሞ በኅብረ ብሔራዊነት ላይ የተመሠረተ፤ በሰላምና መተሳሰብ፣ በፍቅርና ይቅርታ ላይ የተመረኮዘ፤ ከራስ አልፎ ለነገው ትውልድ ታላቅ ሕልምን የሰነቀ ሊሆን ይገባል::

ምክንያቱም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ የሚሹትን ሰላም እና ሁለንተናዊ ብልፅግና እውን ማድረግ የሚቻለው ይሄን መሰል አብሮነት መገንባት ሲቻል እንደመሆኑ፤ አብሮነታችን የሰላምና የሁለንተናዊ ብልጽግናችን አስኳል መሆኑን ተገንዝቦ መሥራት ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ነው!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# በኢፌዴሪ እና ሶማሌ ላንድ መካከል ሁሉን አቀፍ የትብብርና አጋርነት የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል

### / ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የተሰጠ መግለጫ ሙሉ ቃል /

በኢፌዴሪ እና ሶማሌ ላንድ መካከል የተደረገው ስምምነት በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ መስኮች ሰፋ ያሉ የትብብር አድማሶችን ያካተተ ነው። ሶማሌ ላንድ የአፍሪካ ቀርምትን ተከትሎ በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሥር የቆየች ሲሆን እ.ኤ.አ ጁን 26 ቀን 1960 ነፃነቷን አግኝታለች። በወቅቱ በርካታ ሀገራት እውቅና ሰጥተዋት እንደነበርም ይታወሳል። ሆኖም በዚያው ዓመት ከአምስት ቀናት በኋላ በጣሊያን ቅኝ ግዛት ቆይታ ነፃ ከወጣችው ሞቃዲሾ ጋር በፈቃዷ ተቀላቅላለች።

በ1991 እ.ኤ.አ ዳግም ነፃነቷን አውጃ በተከታታይ ሰላማዊ ምርጫ፤ ሰከን ያለ የመንግሥት ቅይይር በማካሄድ ለ30 ዓመታት ዴሞክራሲን በመለማመድ ላይ ትገኛለች። ሀገራችንን ጨምሮ አንዳንድ ሀገራት በሐርጌሳ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ከፍተውም ይንቀሳቀሳሉ:: ነገር ግን እስካሁን የተሟላ ዕውቅና አላገኘችም። ይህም ሆኖ የወደብ አገልግሎትና ልማትን ጨምሮ ከአንዳንድ ሀገራት ጋር ስምምነት ፈርማለች።

ከዚህ ቀደም በርበራ ላይ ለኢትዮጵያ የ19 በመቶ ድርሻ እንዲኖራት ይፈቀድ የነበረ የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሞ እንደነበርም ይታወሳል። በአሁኑ ወቅት ሌሎች ሀገራት ተመሳሳይ ሂደት እየተከተሉ መሆኑም ይታወቃል። ይሄ ሲሆን የተሰማ ኮሽታም ሆነ ቅሬታ አልነበረም። ኢትዮጵያ የወታደራዊ ቤዝና ኮሜርሻል ማሪታይም አገልግሎት በሰጥቶ መቀበልና በኪራይ ለማግኘት የተፈራረመችው የመግባቢያ ሰነድና ሂደትም በመሠረቱ አንድና ያው ነው።

በሀገራችንና በሶማሌ ላንድ መካከል ቆየት ያለ የትብብር ስምምነት ነበረ። ሁለቱ ወገኖች ወዳጅነታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ባደረጉት ጥረት የተገኘው የአሁኑ ሁሉን አቀፍ ትብብርና አጋርነት ሰነድ የሁለቱንም ወገኖች ታሪካዊ የሚባሉ ጥያቄዎችን በሚመልስ፣ ዝርዝር ፣ግልጽና ስትራቴጂክ አጋርነትን በዘላቂነት ለመገንባት የሚያስችል ነው። በሶማሌ ላንድ በኩል ማንም ሀገር እየፈለገ ሊያከውናቸው የማይችሉ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ሲሆን ከማንም ሀገር ሊያገኙት የማይችሉትን እገዛና ሽርክና ያጎናጽፋቸዋል::

የሀገራችንን መሻቶች በተመለከተ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን በግልጽ እንደሰፈረው ለጎረቤቶቻችን ቅድሚያ እንሰጣለን። በዚህም ችግራቸውን ተጋርተን ለመፍትሔው አብረን መሥራት፣ ፀጋዎቻችንን በጋራ በማልማትና በጋራ ተባብሮ ለማደግ ያለንን ራዕይና ጉጉት በተግባር ለመተርጎም ያስችላል። ሕልውናችንን እና ሀገራዊ ጥቅሞቻችንን በአስተማማኝ ለመጠበቅና ለማራመድ የሚያስችል ዕድልም ይፈጥራል።

ሀገራችን በረጅም፣ በመካከለኛና በቅርብ ዘመን ታሪኳ የባሕር በር ባለቤት ነበረች። ከቅርብም ከሩቅም በተሸረበ ተከታታይ ሸፍጥ ተገፍታም የባሕር በሯን አጥታ ነበር። በኋላም በድጋሚ የባሕር በር ባለቤት ሆነች። በስተመጨረሻም ለሦስት አሥርተ ዓመታት በዘለቀና በውስጥ ቀውስና በውጭ ሤራ በታገዘው የእርስ በርስ ጦርነት ተካሂዷል።

በእርስ በርስ ጦርነቱ ማብቂያ ላይም በሕግም በታሪክም ፊት በተፈጸመ ስሕተት የባሕር በር አልባ ሆና ላለፉት 30 ዓመታት ዘልቃለች። ይህንን የታሪክ ስብራትና የትውልድ ቁጭት ለማረም ባለፉት አምስት ዓመታት የለውጡ መንግሥት ከጦርነት በመለስና በሰጥቶ መቀበል መርሕ የሀገራችንን ቁመናና ዕድገት የሚመጥን ዘላቂና አስተማማኝ የወደብና የባሕር በር አማራጮችን ስለማስፋት ሲያውጠነጥንና ሲመክርም ሲሞክርም ቆይቷል::

በያዝነው ዓመት መጀመሪያ ላይ ይኸው ሐሳብ ዳብሮ ለኢትዮጵያውያን እና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ይፋ የመንግሥት አቋም መሆኑ ተበስሯል። መንግሥት ይፋ ባደረገው ይኸው አቋሙ ከማንም ሀገር ጦርነት እንደማይገባና ሁሉንም ወገን ተጠቃሚ የሚያደርጉ አማራጮች መኖራቸውን እንደሚያምን፣ ኢትዮጵያም ያሉዋትን ጸጋዎች ለመጋራት ዝግጁ መሆኗን ሲገልጽ ቆይቷል። በዚሁ መሠረት ጆሮ መስጠት ለቻሉና ለፈለጉ ሁሉ አቋማችንን ለማስረዳት ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን።

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

ከሶማሌ ላንድ ጋር በጋራ ተጠቃሚነት ጉዳዮች ለወራት በብስለትና በስክነት ምክክር እና ድርድር ሲካሄድ ቆይቷል:: እነሆም ሁለቱንም ተጠቃሚ በሚያደርግ አግባብ የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል። ይኸው ሰነድ ለኢትዮጵያ በኤደን ባሕረ ሰላጤ ላይ ዘላቂና አስተማማኝ የባሕር ኃይል ቤዝና ኮሜርሻል ማሪታይም አገልግሎት በሊዝ የምታገኝበትን ዕድል የሚያስገኝ ሲሆን መንግሥት አስቀድሞ ይፋ ባደረገው አቋሙ መሠረት ሶማሌ ላንድ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሊዙ የሚታሰብ ድርሻ እንዲኖራት ያስችላል። ከዚያም ባሻገር በሂደት ሶማሌ ላንድ ዕውቅና ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግሥት በጥልቀት አጢኖ አቋም የሚወስድበትን አግባብም ያካትታል ።

ቀጣናችን የተቸረው ፀጋ ለሁላችንም ከበቂ በላይ ነው። በሥጋት ይሁን በክፋት ተሸብቦ ትብብርን መንፈግ በሕዝቦች ጉስቁልና የሚመነዘር ዝቅታን እንጂ የተሻለ ነገን ለመፍጠር አይቻልም። ከሶማሌ ላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት መንግሥት የኢትዮጵያን መሻቶች ከጎረቤቶቿ ጋር በሚደረግ ትብብር፣ በሰጥቶ መቀበልና በሰላማዊ መንገድ ብቻ ለማሳካት ያለውን እምነት በተግባር ያሳየበት ነው። ይኸው ዕድል ለሁሉም ክፍት የነበረና ክፍት ሆኖም የሚኖር ነው።

ስምምነቱ የኢትዮጵያውያንን የዘመናት ጭንቀትና ቁዘማ ለማከም የሚያስችል አጋጣሚን የፈጠረ ነው። በመሆኑም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያስደስት ታሪካዊ ክስተት ነው። ሁሉም ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሁም የቀጣናው ሠላም የሚገዳቸው የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አባላት ሁሉ ሊደሰቱ ይገባል።

በዚህ ስምምነት የሚጎዳ አካልም ሆነ ሀገር የለም። የተጣሰ ሕግና ተሰበረ እምነትም የለም። እውነታው ይኸው ቢሆንም ማንም እንደሚገምተው በዚህ አወንታዊ ድምዳሜ የሚከፋ፣ የሚደነግጥና ሁኔታውን ለማደፍረስ የሚንቀሳቀስ አካል አይኖርም አይባልም።

በመሆኑም በተለይ ኢትዮጵያውያን በርግጥም ሀገራችን በልኳና በቁመናዋ ልክ በቀጣናው፣ በአህጉራችንና በዓለም አደባባይ ተገቢ ሥፍራዋን ስታገኝ፣ ገንቢ ሚናዋን ስትወጣ፣ ጥቅሞቿንም ስታስከብር ብቻ በጋራ እንደምንከበር ማመንና ለዚህም ልዩነቶችንን ከመቼውም ጊዜ በላይ በማቻቻል ተያይዘን ከፍ እንል ዘንድ ይህን አጋጣሚ እንድንጠቀምበት የኢፌዴሪ መንግሥት ጥሪውን ያቀርባል።

ይህ በዘመናት አንዴ የሚከሠት የታሪክ እጥፋት በመሆኑ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሀገራችንን በጋራ እንታደግ!! ከዘመናት በኋላ በታሪክ የማንወቀስ እንድንሆን ያለንበትን ምዕራፍ ከመወራረፍና ከመጠላለፍ ተላቀን የኢትዮጵያችን ከፍታ ማብሠሪያ ለማድረግ በአንድነት አብረን እንትጋ!!

**ታኅሣሥ 24 ቀን 2016 ዓ.ም አዲስ አበባ**
**የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት**

# ስፖርት አብሮነትን በማጠናከር ረገድ ያለውን ሚና በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡-ስፖርት አብሮነትን በማጠናከር ረገድ ያለውን ሚና በመረዳት በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል ሲሉ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ገለጹ።

የአብሮነት ቀንን ምክንያት በማድረግ “አብሮነትን ለማጠናከር የሚተጋ አመራር” በሚል መሪ ሃሳብ የብልጽግና ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች ሦስተኛውን የማኅበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ትናንት አስጀምረዋል።

በወቅቱ የተገኙት አቶ አደም ፋራህ እንደተናገሩት፤ ስፖርት ለአብሮነት፣ አብሮነትም ለስፖርት ልዩ ትርጉም ስላለው ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን በጋራ መተግበር ይገባል።

ስፖርት በአብሮነት ላይ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ያስችላል ያሉት አቶ አደም፤ ይንን በመገንዘብ ስፖርትን ተጠቅሞ አብሮነትና ብሔራዊ አንድነት የሚያጠናክሩ አስተሳሳሪ ትርክቶችን መገንባት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አደም ገለጻ፤ የአብሮነት ቀን የሚከበረው ስለ አብሮነት ምንነት ፋይዳ ላይ ግንዘቤ ለመፍጠር እንዲሁም አብሮነትን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ሥራዎችን በመሥራት ነው።

በሕዝባችን ዘንድ ያሉትን ድሎች ለማጽናትና የወደፊት ሀገራዊ ራዕይ እውን ለማድረግ የትምህርት ሥርዓቱ ማሳደግና በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ጤናማ ዜጋ ማፍራት ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ አቶ አደም ገለጻ፤ ስፖርቱ በመጠቀም አብሮነትን ማሳደግ እንደሚቻል ሁሉ በትብብር ውስጥ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥና የዳበረ የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት ይቻላል።



በዘመናት የተገኙ ድሎች የአብሮነት ገጸ በረከቶች መሆናቸውን በመገንዘብ በስፖርቱ መንገድ ያሉ አስተሳሳሪ ትርክቶችን ማሳደግ እንደሚገባ አቶ አደም አስረድተዋል።

በስፖርት ውስጥ የሚገነባ አብሮነት የተናጠልና የጋራ ክፍተቶችን ለመሙላትና የጋራ ራዕይ ለማሳካት አስፈላጊ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ዜጎች በተሰማሩበት መስክ ውጤታማ ለመሆን እንዲሁም ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ማሳደግ ይገባል ያሉት አቶ አደም፤ የትምህርት ሥርዓቱ አስተሳሳሪ ትርክት የሚገነባና የሥነ-ምግባር መርሆችን በሕዝብ ዘንድ የሚያሰርጽ መሆን አለበት ብለዋል።

ቀደም ባሉ ጊዜያት የነበሩና አሁንም እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮች ከአብሮነት መላላት የመጡ እንደሆኑ አቶ አደም ጠቁመው፤ መፍትሔውም አብሮነትን ማጠናከር እንደሆነ ገልጸዋል።

የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በበኩላቸው፤ የማኅበረሰብ አቀፍ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ብቁ፣ ንቁና ተወዳዳሪ ዜጎች በማፍራት ረገድ አይነተኛ ሚና እንደሚጫወት ገልጸዋል።

በባለፈው ዓመት የማኅበረሰብ አቀፍ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በአንድ ቀን በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ አምስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዜጎች መሳተፋቸውን አስታውሰው፤ በመላው ሀገሪቱ ስፖርትን ባሕል ያደረገ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አምባሳደር መስፍን ገለጻ፤ በማኅበረሰብ አቀፍ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ “የአንድ ሰዓት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለሚሊዮኖች” በሚል መርሐ-ግብር ዘንድሮ ለሦስተኛ ጊዜ እየተከናወነ ይገኛል።

# በባሕር በር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በቀጣይ የተጠናከረ የዜጎችን ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ቆመው ድጋፍ መስጠትና ለስኬቱ መረባረብ እንደሚገባቸው አመልክተዋል።

ከጎረቤት ሀገራት ጋር የተሻለ ግንኙነትን በመፍጠርና ለጋራ እድገት በመሥራት መሰል ስኬቶችን ለማስመዝገብ እንደሚሠሩም ጨምረው ገልጸዋል።

ከደረቅ ወደብ ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለው የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ወደ ሥራ መግባቱን አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ እና ሶማሌ ላንድ የወደብ ስምምነት ማድረጋቸው የከተማዋን ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያነቃቃ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዚህም የከተማዋን ከንቲባ ጨምሮ ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ዜጎች ሰልፍ በመውጣት ደስታቸውን መግለጫቸውን አስረድተዋል።

የደሴ ከተማ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ ነስረዲን ኃይሌ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ለዓመታት አጥታ የቆየችውን የባሕር በር መጠቀም የሚያስችላት ስምምነት መደረሱ እንዳስደሰታቸው ገልጸዋል።

የባሕር በር አማራጭ ማግኘቷ ለወደፊት ኢኮኖሚያዊ እድገትና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በቀጣይ በሚሠሩት ሥራዎች ሕዝቡ ድጋፍ እንዲያደርግ የማነቃቃትና የማስተባበር ሥራ ይሠራል ብለዋል።

የመግባቢያ ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክር መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይም የጀመረችውን የብልጽግና ራዕይ እውን ለማድረግ ከአጎራባች ሀገራት ጋር የምታደርገውን ሁለንተናዊ ግንኙነት አጠናክራ መቀጠል እንዳለባት ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ባደረገ መልኩ ያደረገችው ስምምነት በጋራ የመልማት ፍላጎትን የሚያመላክት መሆኑን አንስተዋል።

የኢትዮጵያ እና የሶማሌ ላንድን የወደብ ስምምነት ተከትሎ የደሴ፣ ድሬዳዋ፣ ባሕርዳር፣ አሶሳ፣ ወራቤ፣ ሳውላ እና የሌሎች ከተማ ነዋሪዎች ደስታቸውን በሰላማዊ ሰልፍ ገልጸዋል።

በሰላማዊ ሰልፎቹ ላይ የተሳተፉ ዜጎች የኢትዮጵያን የወደብ ስምምነት ወቅታዊና አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን የሚገልጹ ጽሁፎችንና መፈክሮች ቀርበዋል።

በተለያዩ ከተሞች በተካሄዱ የድጋፍ ሰልፎች በሞተር ሳይክልና በተሽከርካሪ የታገዘ ድጋፍ ተካሂዷል፤ ወጣቶች፣ አረጋውያን አካል ጉዳተኞችና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሰልፎቹ ላይ ተሳትፈዋል።

በሌላ በኩል በሶማሌ ላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ የተመራ ልዑክ ትናንት ጅግጅጋ ከተማ የገባ ሲሆን፤ የሶማሌላንድና የሶማሌ ክልል አመራሮች በንግድ፣ በድንበር አካባቢ ባለው የፀጥታ ጉዳይ መክረዋል።

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የሶማሌ ላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲ፣ የፀጥታና የኢኮኖሚ ትብብር የሚያጠናክር የመግባቢያ ስምምነት ሠነድ መፈራረማቸው የሚታወስ ነው።

# በኢትዮጵያና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ መስኮች ሰፊ የትብብር አድማሶችን ያካተተ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

በሀገራችንና በሶማሌ ላንድ መካከል ቆየት ያለ የትብብር ስምምነት ነበረ ያለው መግለጫው፤ ሁለቱ ወገኖች ወዳጅነታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ባደረጉት ጥረት የተገኘው የአሁኑ ሁሉን አቀፍ ትብብርና አጋርነት ሰነድ የሁለቱንም ወገኖች ታሪካዊ የሚባሉ ጥያቄዎችን በሚመልስ፣ ዝርዝር ፣ግልጽና ስትራቴጂክ አጋርነትን በዘላቂነት ለመገንባት የሚያስችል መሆኑን አመላክቷል።

በሶማሌ ላንድ በኩል ማንም ሀገር እየፈለገ ሊከውናቸው የማይችሉ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ሲሆን ከማንም ሀገር ሊያገኙት የማይችሉትን እገዛና ሽርክና ያጎናጽፋቸዋል ሲል አገልግሎቱ ገልጿል።

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ ኢትዮጵያ የነበሯትን ወደቦች ከቅርብም ከሩቅም በተሸረበ ተከታታይ ሸፍጥ ተገፍታም የባሕር በሯን አጥታ ነበር። ይህንን የታሪክ ስብራትና የትውልድ ቁጭት ለማረም ባለፉት አምስት ዓመታት የለውጡ መንግሥት ከጦርነት በመለስና በሰጥቶ መቀበል መርሕ የሀገራችንን ቁመናና ዕድገት የሚመጥን ዘላቂና አስተማማኝ የወደብና የባሕር በር አማራጮችን ስለማስፋት ሲያውጠነጥንና ሲመክርም፤ ሲሞክርም ቆይቷል።

በያዝነው ዓመት መጀመሪያ ላይ ይኸው ሐሳብ ዳብሮ ለኢትዮጵያውያን እና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ይፋ የመንግሥት አቋም መሆኑ ተበስሯል ሲል አስታውቋል።

መንግሥት ይፋ ባደረገው አቋሙ ከማንም ሀገር ጦርነት እንደማይገባና ሁሉንም ወገን ተጠቃሚ የሚያደርጉ አማራጮች መኖራቸውን እንደሚያምን፣ ኢትዮጵያም ያሏትን ፀጋዎች ለመጋራት ዝግጁ መሆኗን ሲገልጽ መቆየቱን አስታውሷል።

ከሶማሌ ላንድ ጋር በጋራ ተጠቃሚነት ጉዳዮች ለወራት በብስለትና በስክነት ምክክር እና ድርድር ሲካሄድ መቆየቱንና በኋላም ሁለቱንም ተጠቃሚ በሚያደርግ አግባብ የመግባቢያ ሰነድ መፈረሙን ጠቁሟል፤

ሰነዱ ለኢትዮጵያ በኤደን ባሕረሰላጤ ላይ ዘላቂና አስተማማኝ የባሕር ኃይል ቤዝና ኮሜርሻል ማሪታይም አገልግሎት በሊዝ የምታገኝበትን ዕድል የሚያስገኝ ሲሆን መንግሥት አስቀድሞ ይፋ ባደረገው አቋሙ መሠረት ሶማሌ ላንድን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሊዙ የሚታሰብ ድርሻ እንዲኖራት ያስችላል ብሏል አገልግሎቱ።

በሂደት ሶማሌ ላንድ ዕውቅና ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግሥት በጥልቀት አጢኖ አቋም የሚወስድበትን አግባብም ያካተተ ስምምነት መደረጉን ገልጿል።

አገልግሎቱ እንዳመላከተው፤ ከሶማሌ ላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት መንግሥት የኢትዮጵያን መሻቶች ከጎረቤቶቿ ጋር በሚደረግ ትብብር፣ በሰጥቶ መቀበልና በሰላማዊ መንገድ ብቻ ለማሳካት ያለውን እምነት በተግባር ያሳየበት ነው። ይኸው ዕድል ለሁሉም ክፍት የነበረና ክፍት ሆኖም የሚኖር ነው።

ስምምነቱ የኢትዮጵያውያንን የዘመናት ጭንቀትና ቁዘማ ለማከም የሚያስችል አጋጣሚን የፈጠረ ነው። በመሆኑም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያስደስት ታሪካዊ ክስተት ነው። ሁሉም ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሁም የቀጣናው ሰላም የሚገዳቸው የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አባላት ሁሉ ሊደሰቱ ይገባል ብሏል።

በዚህ ስምምነት የሚጎዳ አካልም ሆነ ሀገር የለም፤ የተጣሰ ሕግና የተሰበረ እምነትም የለም ያለው የአገልግሎቱ መግለጫ፤ በዚህ አወንታዊ ድምዳሜ የሚከፋ፣ የሚደነግጥና ሁኔታውን ለማደፍረስ የሚንቀሳቀስ አካል አይኖርም አይባልም ሲል አክሏል።

በመሆኑም በተለይ ኢትዮጵያውያን ሀገራችን በመልኳና በቁመናዋ ልክ በቀጣናው፣ በአህጉራችንና በዓለም አደባባይ ተገቢ ሥፍራዋን ስታገኝ፣ ገንቢ ሚናዋን ስትወጣ፣ ጥቅሞቿንም ስታስከበር ብቻ በጋራ እንደምንከበር ማመንና ለዚህም ልዩነቶቻችንን ከመቼውም ጊዜ በላይ በማቻቻል ተያይዘን ከፍ እንል ዘንድ ይህን አጋጣሚ እንደንጠቀምበት ሲል መንግሥት ጥሪውን አቅርቧል።

# “የኢትዮጵያ የባሕር በር ፍላጎት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መርሕን የተከተለ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ከሶማሌ ላንድ ጋር መፈራረሟን ተከትሎ “ግዛታችን ተነካ፣ ሉዓላዊነታችን ተደፈረ” የሚሉ ወገኖች መኖራቸውን ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ፍላጎት ቦታ መንጠቅ አሊያም ሌሎችን መጫን ሳይሆን አብረን ተረዳድተን እንበልጽግ የሚል መሆኑን አንስተዋል። ፍላጎቷ እውን ሲሆን አካባቢው ላይ ቀጣናዊ መረጋጋትን የሚፈጥር ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የብዝኃ ሀገር መሆኗን፤ ማንም ሊጫናት እንደማይችል፤ ሱማሌላንድም አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ግንኙነት መፍጠር የምትፈልግ በመሆኗ ስምምነቱ ለሁለቱም ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር አየለ ገለጻ፤ በሶማሌ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ ያለው ሕዝብ በታሪክ፣ በባሕል የተቆራኘ ነው። የሚቀጥለው ትውልድ ስጋት ውስጥ መግባት ሳይኖርበት በእነዚህ አካባቢ ያሉትን ወደቦች በሥምምነትና ዘላቂ በሆነ መንገድ መጠቀም ይገባል።

ለዚህ ደግሞ ሠላማዊና ጥንቃቄ በተሞላበት ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ ሁሉንም በመግባባት መፍትሔ መፈለግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ይህ ዓላማ ምንም አይነት ጉዳት እንደማያመጣ ለአካባቢው ከዛም አልፎ ለዓለም በሚገባ ማስረዳት ያስፈልጋል ነው ያሉት።

ዶክተር አየለ፤ ኢትዮጵያ ቀይ ባሕር ላይ፣ የኤደን ባሕረ ሰላጤ፣ የሕንድ ውቅያኖስ ላይ መግባቷ የበለጠ ሁሉንም የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አለመሆኑን ገልጸው፤ “ኢትዮጵያ የጦር ሠፈር በመመስረት የመጀመሪያዋ ሀገር አይደለችም። ሌሎች ሀገራትም አሉ። ካላት የሀብትና የሰው ኃይል ቁጥር አንጻር መብቷን ማስከበር አለባት። ሶማሌላንድና ኢትዮጵያ ወደፊት ዘላቂ የሆነ ስምምነት ውስጥ ከገቡ ከስምምነቱ ኋላም ሕዝባዊ ድጋፍ ስላለ ሌሎች ቢቃረኑም ምንም ለውጥ አያመጡም” ብለዋል።

የባሕር በር መጠቀሙ ለማንኛውም ሀገር ማኅበረሰብ አደጋ የማያመጣ እንደሆነና ኢትዮጵያ ያላትን ፍላጎት በተረጋጋና በብልሃት መንፈስ ማሳወቅ ይጠበቃል ሲሉ ገልጸዋል።

“ሆኖም ያሉብንን ብዙ የቤት ሥራዎች አስቀድመን ማጠናቀቅ ይጠበቅብናል። የእርስ በእርስ ግጭት አያዋጣም። አንድነት ሲኖር፣ በአንድ ድምፅ ስንናገር ተሰሚነት ይኖራል ብለዋል። ለዚህ ደግሞ በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የመፈናቀል፣ አፈናና ግጭት ረጅም ለሆነ ዓላማ እንቅፋት እንዳይሆኑ ቶሎ መፍትሔ ሊበጅላቸው ይገባል” ሲሉ መክረዋል።

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከሶማሌላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ ጋር ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ መፈራረማቸው ይታወሳል።

# ወቅታዊ

# ‹‹በምክክሩ ለሌሎች ሀገሮችም ጭምር ተምሳሌት መሆን ይጠበቅብናል››

**አቶ ጥበቡ ታደሰ**
**የኮሚሽኑ ቃል አቀባይ**

*ለምለም መንግሥቱ*

**የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 12/65 2014ዓ.ም ከተቋቋመ ጀምሮ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱ ይታወሳል። ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ሥራዎችን እየሰራ ቢቆይም ወደፊት ግን ሰፊ ሥራ ይጠብቀዋል። የተሰጠው ጊዜ ደግሞ ሶስት ዓመት ነው። ሁለት ዓመት ሲሞላው የቀረው ጥቂት ጊዜ ነው። የሚሰራቸው ሥራዎችና የተሰጠው ጊዜ በቂ ስለመሆኑና አጠቃላይ እንቅስቃሴውን በተመለከተ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚዲያ ኮሙዩኒኬሽንና አጋርነት ዘርፍ አስተባባሪና የኮሚሽኑ ቃል አቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ ጋር ቆይታ አድርገናል።**

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ ኮሚሽኑ እስካሁን ያለፋቸውን ሂደቶች ቢያስታውሱን?**

**አቶ ጥበቡ፡-** የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሥራ ጊዜ የሚቆጠረው ኮሚሽነሮች ተሰይመውለት ሥራውን በይፋ ከጀመረበት ጊዜ መሆኑን በማቋቋሚያ አዋጁ ላይ በግልጽ ተቀምጧል። በዚሁ መሠረትም ኮሚሽኑ ሥራውን ከጀመረ ሁለት ዓመት ሊሆነው የቀረው ጥቂት ጊዜ ነው።

ሥራዎች በአራት ምዕራፍ ተከፍለው እየተሰሩ ሲሆን፤ የመጀመሪያው የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ነው። በዚህ ምዕራፍ ሀገራዊ ምክክር በራሱ ምንነትና ሥራውንም ለማከናወን በአዋጅ የተቋቋመው ኮሚሽን የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች ምንድናቸው? አጠቃላይ የአዋጁስ መንፈስ ምንድነው? የሚለውን የመገንዘብ ሥራዎች ነው ሲሰሩ የነበረው። ምክንያቱም ወደ ሥራ ከመገባቱ በፊት የመጀመሪያው ምዕራፍ ያስፈለገው ምን እንደሚሰራ፣ ለምን እንደሚሰራና እንዴት እንደሚሰራ በአግባቡ መረዳት ይጠይቅ ስለነበር ነው።

ኮሚሽኑ ያሉት በተለያየ የሙያና የትምህርት ዘርፎች ላይ የሚገኙ 11 ኮሚሽነሮች ነው። እነዚህ ኮሚሽነሮች ተግባብተውና ተናብበው ለመሥራት እንዲችሉ እርስ በርሳቸው መተዋወቅ ይኖርባቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ኮሚሽኑ ሥራውን ሲጀምር በነባር ተቋም ሳይሆን፤ በአዲስ መልክ የተቋቋመ ነው። በዚህ ምክንያት የመፈፀም አቅም አልነበረውም። የመፈፀም አቅም እንዲፈጥር የተለያዩ ሥራዎች ሲሰሩ ነበር። እነዚህ በቅድመ ዝግጅት ሥራ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። አጠቃላይ ሁኔታውን የማጤንና የማንበብ የምክክር ሂደቱን በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ የሚያስችሉ ሥራዎች ናቸው።

ሁለተኛው ደግሞ የዝግጅት ምዕራፍ ነው። በዚህም በሃሳብ ደረጃ የተቀመጠና ወደ ሕግም የተቀየረ ነው። ተቋም ተቋቁሞለት ኮሚሽነሮች የሚሰየሙለት ሥራ በምን አግባብ ነው ወደ መሬት ማውረድና መተግበር የሚቻለው በሚሉ ጉዳዮች ላይ ወደትግበራ ከመገባቱ በፊት የዝግጅት ሥራ ያስፈልግ ነበር። አንዳንዶቹ ከቅድመ ዝግጅት ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ ሥራ የዞሩ አሉ። ለምሳሌ የኮሚሽኑን የመፈፀም አቅም የመገንባት ሥራ ይጠቀሳል።

በተጨማሪም ምክክሩ በሂደቱ አሳታፊ፣ አካታችና ግልጽም መሆን አለበት የሚሉ የመሳሰሉ መርሆዎች አሉት። ሰፋፊና ሲተገበሩም ብዙ ጥረትን የሚጠይቁ ናቸው። ስለዚህ በዚህ መርህ መሠረት ምክክሩን ለማካሄድ የሚያስችሉ ነገሮች ለማምጣት ኮሚሽኑ ብቻውን የሚሰራው ሥራ አይሆንም ማለት ነው። ከዚህ አኳያ በሂደቱ ሊሳተፉ የሚገባቸውን የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን የማማከር ሥራ መሥራት ነበረበት።

ምክንያቱም ይሄ ምክክር አሳታፊና አካታች መሆን አለበት ስንል መጨረሻ ላይ በአንድ አዳራሽ ተሰባስበው የአጀንዳ ሃሳቦችን በሚሰጡ ወይንም ደግሞ በምክክሩ በሚሳተፉ ሰዎች ብቻ የሚገለጽ አይደለም። አካታችና አሳታፊ መሆን ያለበት ሂደቱ ሁሉ ነው። ለምሳሌ ተሳታፊዎች በምን አግባብ ቢለዩ ነው የተሻለ የሚሆነው? በሚሉ የተለያዩ ሃሳቦች ላይ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ምክክሮች ተደርገዋል። ይህ ምክክር ከትግራይና አማራ ክልሎች ውጭ በሌሎች ክልሎች ተካሂዷል። በዚህ መልኩ ከኅብረተሰቡ ግብዓት ከተሰበሰበ በኋላ መጨረሻ ላይ ወደ አሰራር ሥርዓት የተቀየረው።


ፎቶ፡- ሒዳሽ አብርሃ

> **ከነዚህ ሁሉ በላይ ግን ይህ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገና ውጤታማም ሊሆን የሚችለው ሃሳቡን ሕዝቡና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሲገዛው ነው**

ስለዚህ በዝግጅት ምዕራፉ ለምሳሌ ተሳታፊዎች በምን መንገድ ይለያሉ ለሚለው ምላሽ ለመስጠት የራሱ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መቅረጽ ነበረበት። ይህን ጨምሮ የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል። ምክክሩ አሳታፊና አካታች መሆን ስላለበት እንዲሁም ኮሚሽኑ ይህን ሰፊ ሥራ ለብቻው የሚወጣው ባለመሆኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር በማድረግ የመግባቢያ ስምምነቶችን የማድረግና አቅምንም የማጎልበት ሥራዎች ተሰርተዋል።

ተቋማዊ አቅምን በሰው ኃይልም በግብዓትም የማጠናከር ሥራዎች በዚህ ምዕራፍ ተጠናክረው የቀጠሉበት ነው። ወደ ተግባራዊ ሂደት የተገባው እነዚህ ዝግጅቶች ከተደረጉ በኋላ ነው። ወይንም ወደ ሶስተኛው ምዕራፍ የተሻገረው። በዚህ የሂደት ምዕራፍ ላይ የሚከናወኑ በርካታ ተግባራት አሉ።

አንደኛው በምክክሩ ውስጥ የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን በአዋጁ ላይ በተቀመጠው መሠረት አካታችና አሳታፊ በሆነ መንገድ የመለየት፤ ሁለተኛ ደግሞ አጀንዳዎችን የማሰባሰብ ሥራ ይጠይቃል። ምክንያቱም በአዋጁ ላይ በእነዚህ አጀንዳዎች ላይ እንመካከራለን፣ በምክክሩ የሚሳተፉ እነዚህ ናቸው የሚል በግልጽ አልተቀመጠም። መርሆዎቹ ናቸው ያሉት። በመርህ ደረጃ ግን ምክክሩ መደረግ ያለበት እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነቶች ወይንም ደግሞ አለመግባባቶች ያላቸው የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ ምሁራንና የፖለቲካ ማኅበረሰቡ መሳተፍ እንዳለበት ብቻ ነው አዋጁ ላይ ደንግጎ የሚያልፈው። አጀንዳዎቹንም በተመለከተ እንዲሁ አቅጣጫ ብቻ ነው ያስቀመጠው። የምንመካከርባቸው ጉዳዮች ሰፊ በመሆናቸው የምንመካከርባቸው ጉዳዮችም እጅግ መሠረታዊና ሀገራዊ መሆን ነው ያለባቸው ተብሎ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ስለዚህ እነዚህ ማለት ምን ማለት ናቸው? አጀንዳዎቹስ ከየት ነው የሚመጡት? የሚሉትን የተቀመጡ አቅጣጫዎችን ይዞ ሥራ መሥራት የሚጠይቅበት ምዕራፍ ነው ማለት ነው። ይሄ የሂደት ምዕራፍ፤ የአጀንዳ ሃሳቦቹ ከተሰባሰቡ በኋላ ከተለያዩ ምንጮች አንድም ከማኅበረሰቡ፤ ሁለተኛ ደግሞ ኮሚሽኑ በራሱ በሚያካሂደው ጥናት፣ ሶስተኛ ደግሞ የተለያዩ አካላት ወይም ከዚህ ቀደም እነዚህ ናቸው ለሀገሪቱ ያለመግባባት የሃሳብ ልዩነቶች ምክንያት ናቸው ብለው ያስቀመጧቸውን ሰነዶች በመፈተሽ፤ ወይንም ደግሞ አሁንም እነዚህ አካላት በቀረበው ጥሪ መሠረት የአጀንዳ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ጭምር ነው ከነዚህ ሁሉ ምንጮች የአጀንዳ ሃሳቦች የሚሰባሰቡት።

በዚህ መልኩ የአጀንዳ ሃሳብ ከተሰበሰበ በኋላ ቀጣዩ የሚሆነው አጀንዳ የመቅረጽ ሂደት ነው። ስለዚህ የሚመጡ በርካታ ሃሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህን ሃሳቦች መልክ የማስያዝ፣ የማደራጀትና ከነዚህም ከመጡ ሃሳቦች መካከል እጅግ መሠረታዊና ሀገራዊ ናቸው የሚባሉትን መለየት ቀጣይ የኮሚሽኑ ሥራ ይሆናል ማለት ነው። ቀጥሎ የሚመጣው ደግሞ ምክክሩ ነው። በምክክሩ መሠረት የተደረሰባቸው መግባባቶች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ምክረ ሃሳብ አዘጋጅቶ መስጠት ቀጣዩ ተግባር ይሆናል ማለት ነው።

አሁን ባለንበት የሂደት ምዕራፍ በዋናነት ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ያለነው የተሳታፊ ልየታ ሥራ ነው። ሌላው ከዚህ ውጭ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራው እነዚህ ሥራዎች የሚመሩበትን የሕግና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ነው። ይህን የሚመለከትም ዘርፍ ተቋቁሟል። ዘርፉ በዚህ ዙሪያ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል።

ከነዚህ ሁሉ በላይ ግን ይህ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገና ውጤታማም ሊሆን የሚችለው ሃሳቡን ሕዝቡና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሲገዛው ነው። ወይም ተቀባይነት ሲኖረው ነው። ተቀባይነት ለማግኘት ደግሞ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች በስፋት ሲሰራ ነው። ከኮሚሽኑ በሚሰነዘሩ ሃሳቦች ብቻ ሳይሆን፤ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚመጡ ሃሳቦችንም በመያዝ ሰፊ የሆነ የማንቃት ግንዛቤ የመፍጠርና ኅብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት የሂደቱ ባለቤት እንዲሆኑ የማድረግ ሥራዎችም እንዲሁ በስፋት እየተካሄደ ነው።

እነዚህን የቅድመ ዝግጅት፣ የዝግጅትና የሂደት ምዕራፎች እንዲሁም ገና በሂደት ላይ ያለው የትግበራ ምዕራፍን ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው፤ ኮሚሽነሮች ተሰይመው ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ዋና ዋና ሥራዎች ተከናውነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ሁለት ዓመት ሲሞላው በቀረው ጥቂት ጊዜ ውስጥ የተለያዩ ሥራዎች መሰራታቸውን ገልጸውልናል። በሥራዎቹ እንደ ጥንካሬ እና ክፍተት የሚነሱትንም ቢያብራሩልን?**

**አቶ ጥበቡ፡-** በተሰሩት ሥራዎች በስኬት ከሚነሱት ውስጥ አንዱ አቅምን ለማጎልበት የተከናወነው ነው። በርግጥ አቅምን ማጎልበት በአንድ ጀንበር የሚጠናቀቅ አይደለም። የሆነ ቦታ ላይም አቅም ተፈጥሯል ይበቃል የሚባልም አይደለም። ኮሚሽኑ ሥራውን እየሰራ ነው

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## ‹‹በምክክሩ ለሌሎች ሀገሮችም ጭምር...

ከገጽ 7 የዞረ

አቅም የሚፈጥረው። ነገሮችን ጎን በጎን በማስኬድ እንጂ አቅም እስኪፈጠር ተብሎ መቀመጥ አይቻልም። ሥራ እየተሰራ የሚፈለገው አቅም እየተገነባ ይሄዳል። ኮሚሽኑ ሲመሰረት ከነበረው አቅም አኳያ በሰው ኃይል፣ በግብዓት፣ በአሰራርና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ሲገመገም ዛሬ ላይ በተሻለ አቋም ላይ ይገኛል:: መሬት ወርዶ ሥራዎችን እየሰራ የሚገኘው አቅም በመፍጠሩም ነው። ውጤት እየተመዘገበ ቢሆንም የመፈፀም አቅሙን አሁን ካለው በላይ ማጎልበት ይኖርበታል።

ሁለተኛው እንደ ስኬት የሚወሰደው ግንዛቤን ለመፍጠር የተሰራው ሥራ ነው። ትናንትና እና ዛሬ ያለው ሁኔታ ፍጹም የተለያየ ነው። በዚህ ላይ የተሰራው ሥራ የተሻለ ነው በሚል የሚወሰድ ቢሆንም ሰፊ ክፍተት እንዳለው በግምገማችን እንገነዘባለን። ክፍተቶችን በመለየት ከውስጥም ከውጭም ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን በመጀመሪያ አካባቢ ላይ የምክክር ኮሚሽኑ ያስፈልጋል ወይ ከሚሉ ጥያቄዎች ጀምሮ ክፍተቶች ነበሩ። በሂደት መግባባትና ልዩነቶችን ወደ ማጥበብ ተመጥቷል። ሀገራዊ ምክክር የሚባለው ጉዳይ በራሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መጥቷል። በተለያዩ ባለድርሻ አካላትና በኅብረተሰቡም ሃሳቦች እየሰረጹ ነው።

አሁን ላይ ተሳታፊዎች የመለየት ሥራ መሥራት የተጀመረው እነዚህ ሁሉ ተግባራት ተከናውነው ነው። ይህም ሥራ ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ድሬዳዋና አዲስ አበባ ከተሞች፣ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሐረሪ እና ሲዳማ ክልሎች ሙሉ ለሙሉ በወረዳ ደረጃ የተሳታፊ ልየታ እና የአጀንዳ ሃሳብ የሚሰጡ ተወካዮችን የማስመረጡ ሂደት ተጠናቅቋል። በአፋርና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የተሳታፊ ልየታ ሥራ ተጠናቅቆ የአጀንዳ ሃሳብ የሚሰጡ ተወካዮች የማስመረጥ ሂደት ላይ ይገኛሉ።

ሶማሌና ደቡብ ክልሎች ላይ ደግሞ ለአጀንዳ ማሰባሰቡ ተወካዮቻቸውን የሚመርጡ ከኮሚሽኑ ጋር ለሚሰሩ ተባባሪ አካላት ስልጠና ተሰጥቶ ዝግጅት ተደርጓል። የተሳታፊ ልየታና የአጀንዳ ሃሳብ የሚሰጡ ተወካዮችን የማስመረጡ ሥራ እየተገባደደ ነው።

ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ከሚኖርባቸውና በርከት ያሉ ወረዳዎች ካሉባቸው ክልሎች አንዱ በሆነው ኦሮሚያ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ካሉት ዞኖች ውስጥ ወደ ስምንት በሚሆኑት ዞኖችና ስድስት ከተሞች ላይ ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር የሚሰሩ ተባባሪ አካላት ሰልጥነው አሁን ላይ ተሳታፊ ልየታ ሂደት ላይ ነው የሚገኙት። በክልሉ የተሰራው ሥራም አሁን በደረስንበት ደረጃ ትልቅ ስኬት ነው ብለን እንወስዳለን። በቀሪዎቹም በተመሳሳይ ተግባራት ይከናወናሉ።

በተጨባጭ ሥራ ውስጥ ያልገባንባቸው የትግራይና የአማራ ክልሎችም ቢሆኑ የተሳታፊ ልየታ ሥራ ስላልተጀመረባቸው እንጂ አስፈላጊ የሆኑ የዝግጅት ሥራዎች ግን እየተሰሩ ይገኛሉ። ተቋማትና ግለሰቦች ኮሚሽኑ ድረስ በአካል በመምጣት የሰጡትንም የአጀንዳ ሃሳብ በማሰባሰብ ረገድም ተጨማሪ ሥራዎች እየተሰሩ በመሆናቸው በዚህ በኩል ያለው ሥራ በውጤት ይገለጻል።

**አዲስ ዘመን፡- አማራና ትግራይ ክልሎች ወደ ኋላ የቀሩት በምን ምክንያት እንደሆነ ቢገልጹልን?**

**አቶ ጥበቡ፡-** መሠረታዊው ጉዳይ የፀጥታ መደፍረስ ነው። ትግራይ ክልል ግን ከጦርነት ውስጥ ወጥቶ አሁን ላይ በማገገም ላይ የሚገኝ እንደሆነ ይታወቃል። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ክልሉ በጦርነቱ የተጎዳ እንደመሆኑ፣ ኅብረተሰቡም ሆነ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ይህ ምክክር ደግሞ አሳታፊና አካታች እንደመሆኑ መጠን ክልሉ ከነበረበት ውጥረት ወጥቶ ኮሚሽኑ የሚሰራቸውን ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል ሁኔታ እስኪፈጠር ነው።

በአማራ ክልል ግን ወደ ሥራ ያልተገባው ግጭት በመኖሩ ነው። እንደሀገር ወደ ምክክር ተገፍተን የገባነውም አለመረጋጋትና ጦርነት በመኖሩ ምክንያት ነው። የሃሳብ ልዩነትና አለመግባባቱ በሰፋ ቁጥር የሚያመራው ወደ ግጭት ነው። ብዙ ታሪካችንም ይህንኑ የሚያሳይ ነው። አለመግባባቶችንና ልዩነቶችን በኃይል አማራጭ ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ማለት ነው። ምክክሩ አሳታፊና አካታች ሆኖ እንዲከናወን ከተፈለገ ቢያንስ አንጻራዊ ሰላም ያስፈልጋል።

ምክክር፤ ጥሞናን፣ መደማመጥን እርጋታን ይፈልጋል። እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች ባልተፈጠሩበት ያለያዩንና ያልተግባባንባቸው ነገሮች አሉ የሚለውን የአጀንዳ ሃሳብ አምጥቶ ተመካክሮ ዘላቂ ሃሳብ ለማምጣት ያስቸግራል። ኮሚሽኑ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ለመወጣት አካባቢው እስኪረጋጋ እየጠበቀ ነው። ለዚህ ምክክር ኮሚሽኑ ብቻ ሳይሆን መንግሥት፣ በግጭት ውስጥ የሚገኙ ወገኖችም ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል።

**አዲስ ዘመን፡- በኦሮሚያ ክልል ያለው ነባራዊ ሁኔታ የኮሚሽኑን ሥራ ለማሳካት የሚያስችል ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ጥበቡ፡-** በክልሉ በተወሰኑ ዞኖች ግጭቶች አሉ። በተወሰኑ ዞኖች ደግሞ አንጻራዊ ሰላም አለ። የምናመጣው ውጤት ተመሳሳይ መሆን እንዳለበት እናምናለን። የሥራ ሂደታችንም ለሁሉም እኩል መሆን አለበት። ግጭት ስላለ አሳታፊነትና አካታችነት መጎዳት የለበትም። እንደየአካባቢው ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን መጠቀም ይኖርብናል ማለት ነው።

በሥራችን ላይ እንደተግዳሮት እየገጠመን ያለው ግጭት ብቻ አይደለም። ለአብነት ለማንሳት አዲስ ክልል የሆኑ አካባቢዎች በሁለት እግራቸው እስኪቆሙ ድረስ ጊዜ ይወስዳሉ። እንዲህ ያለውና ሌላም ምክንያት ነው ለሥራችን መዘግየት ምክንያት እየሆነ ያለው።

ኮሚሽኑ የሚከተለው መርህ ችግሮች ወይንም ግጭቶች ስላሉ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ አያስፈልግም። ኮሚሽኑ ችግሮች አሉ ብሎ ሥራዎችን ሳይሰራ ቀርቶ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራት መፈጸም ባልቻለ ነበር። የእስካሁኑ ሥራም ለቀሪው ሥራ አቅምን አጠናክሮ ለመሥራት ዕድል ይፈጥራል።

**አዲስ ዘመን፡- ለኮሚሽኑ ሥራ እንቅፋት እየሆኑ ያሉት ግጭቶችና የተለያዩ ተግዳሮቶች በእቅዱ እንዳይመራ አያደርጉትም?**

**አቶ ጥበቡ፡-** ምንም ጥርጥር የለውም ሥራን ያጓትታል። አሁንም ለሥራው እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮች አልተወገዱም። ኮሚሽኑ ሥራውን እንዲያጠናቅቅ በአዋጁ የተቀመጠው የሶስት ዓመት ጊዜ ነው። ሆኖም ግን እንዳስፈላጊነቱ የሥራ ጊዜው ሊራዘም ይችላል የሚለው እንደተጠበቀ ነው። ምክክሩ አሳታፊና አካታች ነው። ወረዳ ድረስ ዘልቆ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍልን ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም በሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በዓለም የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያንን ማካተት አለብን ብለን እየሰራን ባለንበት ሁኔታ በሆነ ምክንያት ዘልሎ ሀገራዊ ምክክር ማድረግ አይታሰብም። ምክንያቱም አካታችና አሳታፊ መሆን ስለማይችል ማለት ነው። ይህ ከመሠረታዊ መርሁ አኳያ ሲፈተሸ ተጽእኖ መፍጠሩ አይቀርም።

ኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ተቋቁመው ሥራ ሲጀምር በትግራይ ክልል ጦርነት እየተካሄደ ነበር። የዝግጅትና ሌሎችም ሥራዎች ሲሰሩ የነበረው በዚህ ሁኔታ ነበር። መሬት ላይ ወርዶ ሥራዎች መሥራት በማይቻልባቸው ሁኔታ ነበር ወደፊት ለሚከናወኑ ሥራዎች ሲሰራ የነበረው። ትኩረት ተሰጥቶ ሲሰራ የነበረው ተጽዕኖዎችን ማስወገድ ባይቻል ቢያንስ ሥራው መቆም የማይችልበት ደረጃ ላይ ማድረስ ይቻላል በሚል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ እያከናወናቸው ያሉት ተግባራት ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው? ወይስ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችንም ያካተተ ነው?**

**አቶ ጥበቡ፡-** እጅግ መሠረታዊና ሀገራዊ ጉዳዮቻችንን መፍታት ከቻልን ሌሎች ችግሮች በራሳቸው ሊፈቱ ይችላሉ። ወይም ይከስማሉ። ትልልቆቹ ችግሮች ሲፈቱ አብረው ሊፈቱም ይችላሉ። ካለው ጊዜ አንጻርም ከፍተኛው ላይ ማተኮሩ የተሻለ ነው። አሁን ላይ ሆነን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘት ያላቸው መሆናቸውን ማወቅ አንችልም። ወደፊት በሚሰበሰቡት የአጀንዳ ሃሳቦችና ኮሚሽኑ ደግሞ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት አጀንዳዎች በሚቀረጹበት ወቅት የሚታወቅ ነው የሚሆነው። ነገር ግን ገዥው ነገር እጅግ



መሠረታዊና ሀገራዊ ጉዳይ መሆን አለባቸው ነው።

ኅብተሰብንም ሆነ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ያስፈለገውም፤ የአጀንዳ ሃሳቦቻችንን ከሥር ከመሠረቱ ማውጣት ወይንም መለየት አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ከዚህ ቀደም በነበረው ተሞክሮ ይመለከታቸዋል በተባሉ በተወሰኑ አካላት አጀንዳዎች ተቀምጠው ውይይት ተደርጎ ነበር። ውይይቱ እንደ አሁኑ ኮሚሽኑ እንደተከተለው አቅጣጫ ስፋትና ጥልቀት አልነበረውም። አንዱ የማንግባባት ጉዳይ በአጀንዳዎቻችን ላይ ጭምር ነው። ለአንዱ ትልቅ ጉዳይ የሆነው ለሌላው ደግሞ ላይሆን የሚችልበት አጋጣሚ አለ። መግባባቱ መፍጠር ያለበት ከአጀንዳ ቀረፃ ጀምሮ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በተለያየ ዓለም ላይ የሚኖረውን ዳያስፖራ በምን መልኩ ነው ተደራሽ እንዲሆን እየተሰራ ያለው?**

**አቶ ጥበቡ፡-** በሀገሩ ጉዳይ ላይ ይመለከተኛል የሚል በየትኛውም ዓለም የሚኖር ሁሉ ተሳታፊ እንዲሆን ነው የሚፈለገው። ልክ ሀገር ውስጥ እንደሚከናወነው ሁሉ ዳያስፖራውም እንዲሳተፍ በእቅድ እየተሰራ ነው። የትኩረት ቦታ ተብለው የተለዩ አሉ። አንዱ ወረዳዎችን ጨምሮ ክልልና ከተማ አስተዳደሮች፣ሁለተኛ ደግሞ በፌዴራል ደረጃ ነው። ሶስተኛው ዳያስፖራዎች ናቸው።

ዳያስፖራ ወገኖቻችን በምን ሁኔታ ቢሳተፉና ቢካተቱ የተሻለ ይሆናል የሚለውን ከእነርሱ ጋር እየተመካከርን ነው። እስካሁን ባለውም በአፍሪካ፣ በአውሮፓ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር በበይነመረብ (ኢንተርኔት) አማካኝነት ምክክር እየተደረገ ነው። ስለሀገራዊ ምክክሩ ግንዛቤ መፍጠር፣ ስለኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነትም የማስተዋወቅ፣ ወይም ማስረዳት ጭምር በምን መልኩ ማሳተፍ እንደሚቻል ግብዓት ከእነርሱ በመወሰድ ጭምር እየተሰራ ነው። በተመሳሳይ በሌሎች ሀገሮች ከሚኖሩ ዳያስፖራዎች ጋርም ሥራው ይቀጥላል።

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ የያዘው ሥራ ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተሰጠው ጊዜ በቂ ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ጥበቡ፡-** የሆነ ሥራ ተሰርቶ የሆነ ነገር ላይ የሚቆም ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ልዩነቶቻችንና የማያግባቡንን ነገሮች በምክክር የመፍታት ባህል ልናዳብር ይገባል። እንዲህ ያለውን ባህል ኮሚሽኑ ለሶስት ዓመት በሚሰራው ሥራ ብቻ ማምጣት አይቻልም። ያሉት ችግሮች ውስብስብና ለዘመናትም የተከማቹ ናቸው። አሁንም የቀጠሉ በመሆናቸው በአንድ ጊዜ እልባት ላይ ላይደርስ ይችላል። ጊዜ ይጠይቃል።

ኮሚሽኑ በተሰጠው ጊዜና በአዋጅም በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ተልዕኮውን ለመወጣት በተቻለው መጠን ጥረት እያደረገ ይገኛል። ሆኖም ግን በእቅዱ መሠረት መፈፀም ካልተቻለ ሕጉ ክፍት ነው። ሕጉን ያወጣው አካል ወይንም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኮሚሽኑ ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልገዋል ብሎ ካመነ የማራዘም ሥልጣን አለው። የጊዜው ጉዳይ በአንድ በኩል ያሳስባል። ምክንያቱም ተጨማሪ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ሥራዎች ቶሎ ቶሎ መሠራት አለባቸው።

በሌላ በኩል የተጀመረው የምክክር ሥራ በማያዳግም ሁኔታ መሠራት ስላለበት በጥንቃቄና በእርጋታ መሠራት ይኖርባቸዋል። የኮሚሽኑ ሥራ እዚህም እዛም የሚፈጠሩ ግጭቶችን ማስቆም አይደለም ተልዕኮው፤ ለግጭት መንስኤ የሆኑትንና ሌሎችንም ችግሮች ከሥር ከመሠረቱ በማጥናት ዘላቂ መፍትሔ እንዲመጣ ማስቻል ነው። ይህ ደግሞ ጊዜ ይጠይቃል።

በጥቅሉ እየተሰራ ባለው ሥራ ውጤታማ ነው ውጤታማ አይደለም ብሎ ለማስቀመጥ ብቻ አይደለም። ሂደቱ በራሱ ወሳኝ ነው። በሂደቱ ውስጥ ልምድ እየተገኘ ነው። አቅምም እየተፈጠረ ነው። ችግሮች ሲያጋጥሙ የምንፈታባቸው ጥሩ የሆኑ የባህል እሴቶች አሉን፤ ነገር ግን እንደ ሀገር በአዋጅ ተቋቁሞ የተለያዩ አካላትን በማሳተፍ በስፋትና በጥልቀት መንቀሳቀስ የተለመደ አይደለም። ይህ መልካም ጅምር ተደርጎ ይወሰዳል። በዚህ ሂደት ማለፍ እንደ ሀገር ትልቅ ዕድልም ነው።

እየተሰራ ባለው ሥራ ፈጣን የሆነ ውጤት ማስመዝገብ ባይቻልም። ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ የተሰሩት ሥራዎች ተስፋ የሚሰጡ ናቸው። ጊዜ ቢወስድም በጠረጴዛ ዙሪያ ምክክሩ መካሄዱ አይቀሬ በመሆኑ መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም ዝግጁነቱን ማሳየት ይጠበቅበታል። በምክክሩ ለሌሎች ሀገሮችም ጭምር ተምሳሌት መሆን ይጠበቅብናል። በኮሚሽኑ አካሄድ ላይ ጥያቄዎች ካሉ በግልጽ ማቅረብ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ጥበቡ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# በስኳር ምርት ራስን የመቻል አዲስ ጥረት

**አንተነህ ቸሬ**

ኢትዮጵያ ለስኳር ልማት ዘርፍ ትልቅና እምቅ አቅም አላት:: ሀገሪቱ ዘርፉን ለማስፋፋትና ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚያስችል ከፍተኛ የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትም ናት:: በተለይም ለሸንኮራ አገዳ ልማት ተስማሚ የሆነው የአየር ንብረቷ፣ በመስኖ ሊለማ የሚችል እስከ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሔክታር የሚደርስ ሰፊ የእርሻ መሬቷ እንዲሁም ‹‹የአፍሪካ የውሃ ማማ›› ያሰኛት በቂ የውሃ ሀብቷ፣ በስኳር ልማት ዘርፍ ከፍተኛ ውጤት እንድታስመዘግብ የሚያስችሏት አጋዥ ግብዓቶች ናቸው::

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የስኳር ኢንዱስትሪ ልማት የተጀመረው በ1943 ዓ.ም ነው:: በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ‹‹ኤች. ቪ.ኤ›› (HVA) ከተባለ የኔዘርላንድስ ኩባንያ ጋር የአክስዮን ስምምነት በመፈራረም ዘመናዊ የስኳር ልማት ሥራ እንዲጀመር አድርጓል:: ኩባንያው ሥራውን የጀመረው አምስት ሺ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማልሚያ መሬት ተረክቦ ሸንኮራ አገዳ በማልማትና ‹‹የወንጂ ስኳር ፋብሪካ››ን በመገንባት ነበር::

ኢትዮጵያ ለስኳር ልማትና ንግድ አዋጭ መሆኗን የተረዳው ይኸው ኩባንያ፣ የ‹‹መተሐራ›› ስኳር ፋብሪካን ደግሞ በ1962 ዓ.ም ገንብቶ ሥራ አስጀመረ:: በመቀጠልም ‹‹ቡከርስ አግሪካልቸራል ኢንተርናሽናል ሊሚትድ›› የተባለው የእንግሊዝ ኩባንያ በፊንጫአ አካባቢ ዝርዝር የስኳር ልማት ጥናት አደረገ:: በጥናቱ መሠረት ‹‹ኤፍ.ሲ.ሼፈርና አሶሽየትስ›› እና ‹‹ድዌቶ ኢንተርናሽናል›› የተባሉ የአሜሪካና የኔዘርላንድስ ኩባንያዎች እንዲሁም በርካታ ሀገር በቀል ድርጅቶች ባከናወኑት የፋብሪካና ኤታኖል ማምረቻ ግንባታ አማካኝነት፣ በ1991 ዓ.ም የ‹‹ፊንጫአ›› ስኳር ፋብሪካ የምርት ሥራ እንዲጀምር ተደረገ::

የስኳር ልማትን የማሳደጉ ጥረት ቀጥሎ፣ በምርትና በግንባታ ላይ በሚገኙት ሌሎች የስኳር ፋብሪካዎች (‹‹ተንዳሆ››፣ ‹‹አርጆ ዲዴሳ››፣ ‹‹ከሰም››፣ ‹‹ጣና በለስ›› ‹‹ኦሞ ከራዝ›› እና ‹‹ወልቃይት›› ፋብሪካዎች) አማካኝነት ሀገሪቱን የስኳር ፍላጎት ለማሟላት ዘርፈ ብዙ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል::

የፋብሪካዎቹ የአስተዳደር ሁኔታም ከሀገሪቱ የመንግሥታት መለዋወጥ ጋር እየተለዋወጠ ዘልቋል:: በወታደራዊው መንግሥት ዘመን የስኳር ፋብሪካዎቹ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ይዞታ ስር ሆነው፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 58/1970 የተቋቋመው ‹‹የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን›› ፋብሪካዎቹን ያስተዳድር ነበር::

ከ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በኋላ ‹‹የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን›› በሕግ ፈርሶ፣ ፋብሪካዎቹ ራሳቸውን የቻሉ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሆነው እንዲቋቋሙ ተደረገ:: በ1990 ዓ.ም ደግሞ ‹‹የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል አክስዮን ማኅበር›› የተሰኘ ድርጅት ለስኳር ፋብሪካዎቹ የጋራ አገልግሎት እንዲሰጥ ተቋቋመ:: ከስምንት ዓመታት በኋላ ደግሞ በዚህ ማዕከል ምትክ ‹‹የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ›› በአዋጅ ቁጥር 504/98 ተመስርቶ የስኳር ፋብሪካዎቹን በመቆጣጠር፣ በፕሮጀክት ልማት፣ በምርምር፣ በስልጠናና በግብይት ረገድ ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል::

ኤጀንሲው በ2003 ዓ.ም ፈርሶ፣ ‹‹ስኳር ኮርፖሬሽን›› በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 ተቋቋመ:: በፕሮጀክት አፈፃፀምና በገንዘብ አስተዳደር ረገድ አነጋጋሪ የነበረውና በርካታ ጥያቄዎች የተነሱበት ኮርፖሬሽኑ በመጋቢት 2014 ዓ.ም ፈርሶ፣ ‹‹የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ›› ተቋቁሟል::

ኢትዮጵያ ለስኳር ልማት ዘርፍ ትልቅና እምቅ አቅም ያላት ሀገር ብትሆንም፣ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን የስኳር ፍላጎቷን የምታሟላው ከውጭ በመግዛት ነው:: የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ በአሁኑ ወቅት ያለው አጠቃላይ ዓመታዊ ሀገራዊ የስኳር አቅርቦት መጠን ከአምስት ሚሊዮን እስከ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ነው:: ከዚህ ውስጥ ባለፉት ዓመታት በዓመት ከሦስት እስከ አራት ሚሊዮን ኩንታል የሚደርስ ስኳር በሀገር ውስጥ የተመረተ ሲሆን፣ በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለው ከአንድ ሚሊዮን እስከ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የሚደርስ ስኳር በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በየዓመቱ ወደ ሀገር ውስጥ እየገባ ይገኛል:: በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የአንድ ሰው ዓመታዊ የስኳር ፍጆታ ከ10 ኪሎ ግራም በላይ እንደሚደርስ ቢገመትም፣ እየቀረበ ያለው መጠን ግን ስድስት ኪሎ ግራም ያህል ነው::

ምንም እንኳ ኢንዱስትሪው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ እድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም፤ በኢንዱስትሪው በሚፈለገው ፍጥነት አለማደግ፣ ሀገሪቱ በተከታታይ ባስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት የኅብረተሰቡ የስኳር ፍላጐት በከፍተኛ ደረጃ መጨመር፣ ነባር የስኳር ፋብሪካዎች የሚያመርቱት የስኳር መጠን እያደገ የመጣውን የሀገር ውስጥ ፍላጎት ማርካት አለመቻሉ፣ የሕዝብ ቁጥር ማደግ እና ስኳርን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ መስፋፋት ለስኳር ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ዋና ዋና ምክንያቶች ተደርገው ይጠቀሳሉ::

**በርካታ የስኳር ፋብሪካዎችን በአንድ ጊዜ ለመገንባት ተጀምሮ የነበረው እቅድ ሀገሪቱን ለከፍተኛ ኪሳራ ዳርጓታል፡፡ በስኳር ልማት ዘርፍ ላይ የተጋረጡ በርካታ መሰናክሎች ቢኖሩም የግብዓት አቅርቦት፣ የፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ እጥረት፤ የአመራር ድክመት እንዲሁም ከንግድና ግብይት ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮች የሀገሪቱ አቅምና የማምረት መጠን እንዲራራቅ ያደረጉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡**

በርካታ የስኳር ፋብሪካዎችን በአንድ ጊዜ ለመገንባት ተጀምሮ የነበረው እቅድ ሀገሪቱን ለከፍተኛ ኪሳራ ዳርጓታል:: በስኳር ልማት ዘርፍ ላይ የተጋረጡ በርካታ መሰናክሎች ቢኖሩም የግብዓት አቅርቦት፣ የፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ እጥረት፤ የአመራር ድክመት እንዲሁም ከንግድና ግብይት ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮች የሀገሪቱ አቅምና የማምረት መጠን እንዲራራቅ ያደረጉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው:: በመሆኑም ሀገሪቱ ለስኳር ልማት ያላትን እምቅ አቅም በተገቢው ደረጃ ጥቅም ላይ ለማዋል መንግሥት አምስት የስኳር ፋብሪካዎችን (ወንጂ ሸዋ፣ መተሐራ፣ ከሰም፣ ጣና በለስ እና ፊንጫአ) በአዋጅ ቁጥር 500/2014 ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ አድርጓል::

ይህ የመንግሥት ርምጃ ፋብሪካዎቹ ያሉባቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዲቃለሉና በተሻለ አቅም እንዲያመርቱ እድል በመፍጠር፣ የስኳር ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣምን ለማስተካከል የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያግዝ ታምኖበታል:: በዚህ ርምጃም አንዳንድ ፋብሪካዎች ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማየት ጀምረዋል:: በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ከሆኑት ፋብሪካዎች መካከል አንዱ ‹‹ወንጂ ሸዋ›› ስኳር ፋብሪካ ነው::

በኢትዮጵያ ግንባር ቀደም የሆነው ፋብሪካው፣ በዓመት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ስኳር እና 31 ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም አለው:: ይሁን እንጂ አሁናዊ የምርት አቅሙ ከ300ሺ ኩንታል ብዙም የተሻገረ አይደለም::

የፋብሪካው ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጀማል አማን እንደሚገልፁት፣ ስኳር ፋብሪካዎች ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ ከተወሰነ በኋላ የፋብሪካው ሥራ አመራር ቦርድ ለፋብሪካው ምርታማነት ማደግ ዘርፈ ብዙ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል:: ዘንድሮ 327ሺ ኩንታል ለማምረት ያቀደ ሲሆን፣ በ2017 የምርት ዘመን ደግሞ አንድ ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ለማምረት አቅዷል::

‹‹ፋብሪካው በ2007 ዓ.ም አንድ ሚሊዮን 158ሺ ኩንታል ስኳር አምርቷል:: በአሁኑ ወቅት እያመረተ ያለው ግን ከ300ሺ እስከ 400ሺ ኩንታል ብቻ ነው፤ ይህ ደግሞ ፋብሪካው ካለው አቅም 31 በመቶ ብቻ ነው›› ሲሉ ዋና ሥራ አስኪያጁ ይገልጻሉ:: የዚህ ምክንያቱ የአገዳ ሽፋኑ በሚፈለገው ልክ በቂ አለመሆኑ ላይ እንደሆነም ይጠቅሳሉ:: ችግሩ ለቦርድ ቀርቦ ቦርዱም ድጋፍ አድርጎ የአገዳ ሽፋኑን የማሳደግ ሥራ እየተሰራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ መሠረተ ልማቶችን የማደስ ተግባራትም ተከናውነዋል:: የፋብሪካውን የምርት መጠን የሚወስነው የአገዳ አቅርቦት ነው:: መንግሥት እያደረገ በሚገኘው ድጋፍ አማካኝነት ፋብሪካው በ2017 አንድ ሚሊዮን ኩንታል ስኳር የማምረት እቅዱን ለማሳካት ጥረት እያደረገ ነው::

ፋብሪካው ከስኳር ምርት በተጨማሪ በሌማት ትሩፋት መርሃ ግብርም በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ አቶ ጀማል ይጠቁማሉ:: በፋብሪካው አማካኝነት ሰፋፊ የስንዴ ልማት ሥራዎች ተሰርተዋል:: በዘመናዊ የከብት ማድለቢያው ባለፈው ዓመት 500 ከብቶችን አድልቦ ለገበያ ማቅረቡን ጠቅሰው፤ ዘንድሮም በመጀመሪያው ዙር ከ300 በላይ ከብቶችን እያደለበ ነው:: ከሶስት ሺ 500 በላይ ዶሮችንም እያረባ ይገኛል ብለዋል::

«የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ» ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አብዱራህማን ኢድ በበኩላቸው፣ ፋብሪካዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲደራጁ ከተደረገ ወዲህ ተጨባጭ ለውጥ ካሳዩ ፋብሪካዎች መካከል «ወንጂ ሸዋ›› ስኳር ፋብሪካ አንዱ መሆኑን ገልጸዋል:: እሳቸው እንዳሉት፤ የፋብሪካው የምርት መጠን እየተሻሻለ ነው፤ በ2017 አንድ ሚሊዮን ኩንታል ለማምረት የተያዘውን እቅድ ለማሳካት የአገዳ ምርትን የማሳደግ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል::

ፋብሪካው ባለው የራሱ ስድስት ሺ ሄክታር መሬት ላይ ከሚያለማው ሸንኮራ አገዳ በተጨማሪ ከአርሶ አደሮች ጋር በገባው ውል አማካኝነት ያገኝ የነበረውን የአገዳ ምርት በሚፈለገው ልክ አለማግኘቱ በምርቱ ላይ ተፅዕኖ ፈጥሮበት መቆየቱን ዋና ሥራ አስፈጻሚው አስታውቀዋል:: የአመራር ማስተካከያ በማድረግ የፋብሪካዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል ጥረት መደረጉንም አቶ አብዱራህማን ጠቅሰው፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ፋብሪካዎቹ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የመፍትሔ አማራጮችን በማስተባበርና በማቀናጀት እገዛ እንደሚያደርግም ገልጸዋል::

ሀገሪቱ ለስኳር ልማት ያላትን እምቅ አቅም በተገቢው ደረጃ ጥቅም ላይ ለማዋል አምስት የስኳር ፋብሪካዎችን (ወንጂ ሸዋ፣ መተሐራ፣ ከሰም፣ ጣና በለስ እና ፊንጫአ) ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ ሲወሰን ከተተገበሩ አሰራሮች መካከል አንዱ ፋብሪካዎቹ የየራሳቸው የሥራ አመራር ቦርድ እንዲኖራቸው መደረጉ ነው:: የሥራ አመራር ቦርዶቹ የፋብሪካዎቹ ችግሮች በጥናት እንዲለዩ በማድረግ ችግሮቹ የሚፈቱበትን መንገድ እያመቻቹና ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ::

የኦሮሚያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ አቶ አወሉ አብዲ፣ የፋብሪካው ችግሮች በጥናት ተለይተው ለችግሮቹ የመፍትሔ አቅጣጫዎች መቀመጣቸውን ይገልፃሉ:: ‹‹‹ፋብሪካው ሰፊ የሆነ መሬትና የሰው ኃይል አለው:: ነገር ግን በሙሉ አቅሙ እንዳያመርት መሰናከል የሆኑበት ችግሮች ምን እንደሆኑ ለመለየት በባለሙያዎች ዝርዝር ጥናት ተደርጓል›› ሲሉም ተናግረዋል::

የቦርዱ ሰብሳቢ እንዳሉት፤ ከችግሮቹ መካከል አንዱ የአመራር ድክመት ነው:: ከቦርድ እስከ ታችኛው ፈፃሚ ድረስ፣ በየደረጃው ያለው አመራር ችግሮቹን ለይቶና አውቆ ፋብሪካውን በመምራትና በማስተዳደር ረገድ መጠነ ሰፊ የአቅም ውስንነት ይታይበት ነበር:: የድጋፍና ክትትል ውስንነት እንዲሁም አርሶ አደሩን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ችግር ነበር:: ለማሳ ዝግጅትና ከእንክብካቤ፣ ለማዳበሪያ፣ ለውሃና ለሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት የተሰጠው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ ነበር::

ችግሮቹን በመሠረታዊነት ለመፍታት ከአርሶ አደሩ ጋር በመወያየት የግብዓት አቅርቦት እንዲሻሻል መደረጉን አቶ አወሉ አስታውቀዋል:: ‹‹የፋብሪካውን አቅም ባገናዘበ መልኩ ለሠራተኛው ማበረታቻ ተሰጥቷል:: በዚህም ለሌሎች ፋብሪካዎችም ተሞክሮ ሊሆኑ የሚችሉ እና ኢንዱስትሪውን መሠረታዊ በሆነ መልኩ ለመቀየር የሚስችሉ ጅምር ውጤቶች ተገኝተዋል›› ሲሉም ገልጸዋል:: እነዚህን ተግባራት አጠናክሮ ማስቀጠል ከተቻለ፤ አርሶ አደሩም ሆነ የፋብሪካው ማኅበረሰብ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን እና በ2017 አንድ ሚሊዮን ኩንታል የማምረት እቅድን ማሳካት እንደሚቻል አቶ አወሉ አስታውቀዋል::

# ጎሜ

# ገናን ማን ያክብረው?

**ምሕረት ሞገስ**

ብዙ ጭንቀቶች እያለፉም ቢሆን ሕይወት ይቀጥላል። ተሰማ መንግሥቴ፣ ገብረየስ ገብረማሪያም እና ዘውዴ መታፈሪያ አንዳንዴ በየተራ ብዙ ጊዜ ደግሞ በአንድ ላይ ብዙ የጭንቀት ጊዜዎችን አልፈዋል። አንድ ሰሞን ተሰማ ስለ ቤተሰቡ ስለ ዘመዶቹ በአጠቃላይ ስለ ሀገሪቷ ሁኔታ አብዝቶ ሲጨነቅ ነበር። በሌላ በኩል አንድ ሰሞን ገብረየስም ስለ ዘመዶቹ በተለይም ትግራይ አካባቢ ስላሉ ወገኖቹ አብዝቶ ሲያዝን እና ሲያለቅስ ነበር። የዘውዴ ደግሞ ተደጋጋሚ ነው። ዘውዴ ጭንቀቱ ቀለል የሚልለት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው። በአብዛኛው ስለራሱ እና ስለቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን ስለአጠቃላይ የሀገሪቱ ሁኔታ አብዝቶ በተደጋጋሚ ይጨነቃል።

ሰሞኑን ምንም እንኳ በበዓል ሰሞን መደሰት ቢኖርባቸውም ሶስቱም ጭንቀት ውስጥ ናቸው። እንደልማዳቸው በማምሻ ግሮሰሪ ተገናኝተዋል። የበዓል ሰሞን በመሆኑ ግሮሰሪው ሞቅ ብሏል። እነርሱ ግን ተጨንቀዋል። ገብረየስ ‹‹ወገኖቼ በርሃብ ሊያልቁ ነው›› ብሎ ይብከነከናል። ተሰማም ‹‹ዘመዶቼ በዘራፊዎች እየተሰቃዩ ከነገ ዛሬ ታፍነው ገንዘብ እጠየቃለሁ›› ብሎ ስጋት ውስጥ ገብቷል። ዘውዴም በየቀኑ ቀያቸው አካባቢ ባለው ችግር ሳቢያ እከሌ ሞተ እየተባለ የሚሰማው ዜና ከዕለት ወደ ዕለት እርሱን የተለየ ዕብደት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል።

ሶስቱም ማምሻ ግሮሰሪ ተገናኝተው ጭንቀታቸውን አንዱ በሌላው ላይ ይተነፍሳል። አሁን ግን አንዱ ታግሶ የሌላውን እያዳመጠ አይደለም። አንዱ ሲናገር ሁሉ ይሰማል፤ ሁሉ ሲናገር ማን ይሰማል? ይባላል። ይህ መደማመጥ እና መግባባት እንዲኖር ተራ ጠብቆ ማውራት ይገባል ለማለት ያህል ቢሆንም፤ እነተሰማ ግን በየራሳቸው ጭንቀት ውስጥ ተወጥረው ከመናገር ይልቅ ዝምታን መርጠው መቆዘሙን ተያያዙት።

ነገር ግን ዝምታቸውም ብዙ አዋጭ አልሆነላቸውም። ሶስቱም የውስጥ ጭንቀታቸው ከሚጠጡት ቢራ ጋር ተቀላቅሎ ሶስቱም ራሱን እንዳመመው ሰው ፊታቸው አብጦ ዓይናቸው ተንጠልጥሎ የተከፋው ፊታቸው የተደሰተ ሰውን ከማስጨነቅ አልፎ ያስኮርፋል። ለተሰማ ቢራ የከፈተው አስተናጋጁ ይርጋ ‹‹ በዓል እኮ ነው፤ ምነው ተከዛችሁ?›› ብሎ ጠየቀ። ዘውዴ ‹‹የምን በዓል ነው? እኛ በእውነት እግዚአብሔርን መውደድ የማንችል ሰዎች የፈጣሪን የኢየሱስ ክርስቶስን የመወለድ በዓል ለምን እናከብራለን? ›› ሲል ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ። ይርጋ ለመመለስ አቅሙም ጊዜውም ስላልነበረው መሰስ ብሎ ወደ ሥራው ተመለሰ።

ገብረየስ የዘውዴን ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ መናገር ጀመረ። ‹‹ በርግጥም ኢትዮጵያውያን ስለ እግዚአብሔር ደጋግመን እንናገራለን። ነገር ግን ድርጊታችን እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው የሚፈፅመው አይደለም። እንደውም ብዙዎቻችን በአፍ እንጂ ከልብ በመነጨ ስሜት እግዚአብሔርን የምንወደው አይመስለኝም። የማንወደው ከሆነ ደግሞ ጓደኞቻችንን እና በአጠቃላይ የሰው ልጆችን ሙሉ በሙሉ መውደድ አንችልም። ከሰማይ ወርዶ በጠባብ ማሕፀን የተወሰነው ፈጣሪ ግን፤ የተወለደበት ትልቁ ምክንያት ሀጢያተኛውን የሰውን ልጅ ለማዳን ነው። የርህራሄና የፍቅር አምላክ የሆነው ጌታ የመወለዱን ልደት ለማክበር ቀድመን እግዚአብሔርን መውደድ እና ስለ ሰው ልጅ ፍቅር ራሳችንን መግዛት ይኖርብናል። ሰው ሆኖ የሰውን ልጅ ከዘላለም ሞት የታደገውን አምላክ ልደቱን ለማክበር እኔም ብቁ ነኝ ብዬ አላምንም።›› ሲል ሃሳቡን ገለጸ።

ዓይኑን ቡዝዝ አድርጎ ፈዞ የገብረየስን ንግግር

> **እኛ እኮ እግዚአብሔርን እንወዳለን እያልን የአምላክን ልደት ለማክበር የምንሞክር ደፋሮች ብንሆንም፤ እውነታው ግን ደካሞች ላይ የምንበረታ ጨካኞች፤ የሞተን ሰው እንኳ ይቅር ለማለት የምንቸገር ግብዞች፤ አልፈን ተርፈን የሞተን የምንሰቅል አረመኔዎች ነን**

ሲያዳምጥ የነበረው ዘውዴ፤ ‹‹ አይ ገብረየስ እኛን ክፉዎቹን ክርስቶስን ለመስቀል የተፎካከርን ግብዞች የእኛን ፍቅር ከክርስቶስ ፍቅር ጋር ታነፃፅረናለህ? ›› ሲል ጠየቀና ሃሳቡን ቀጠለ። ‹‹ ክርስቶስ ለእኛ ሲል ፍፁም ሰው ሆኖ የእኛን መከራ ሊቀበል ከመወለድ በተጨማሪ በሽተኛዎችን ሲፈውስ፣ የተጨቆኑትን ከፍ ሲያደርግ፣ በበጎነት ሲመላለስ፣ ትዕግስትን ሲያስተምር፣ ራስ ወዳድ አለመሆንን ሲያሳይ እና ሲሰብክ፣ በመጨረሻም ይቅር ባይነቱን በመስቀል ላይ ሆኖ የሰቀሉትን ወንበዴዎች ጨርስልኝ እንደማለት ‹የሚያደርጉትን አያውቁትምና፤ ይቅር በላቸው› ያለ የፍቅርን ጥግ ያሳየ አምላክ ነው። እኛ ግን እርስ በእርስ በምናደርገው የቀን ተቀን ግንኙነቶች ውስጥ ሳይቀር ከፍቅራችን ይልቅ ጎልቶ የሚታየው ብዙ ሰዓት የሚይዘው ጠባችን ነው። የእኛ መገለጫ ባህሪያቶች ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

በሁሉም ግንኙነቶቻችን ውስጥ በተለይም ከግለሰባዊ ባሻገር በቡድናዊ ግንኙነት ውስጥ የምናሳያቸው ባህሪዎች በልባችን ውስጥ ፍቅር እንዳለ የሚያሳዩ አይደሉም። ሰው ሆነን ደግ ሆኖ ሰዎችን ከመርዳት በተቃራኒው ባልሰሩት ጥፋት ሰዎች ሲቀጡ ቅንጣት ፀፀት የማይሰማን ጨካኞች፤ ትንሽ ደግነት እንኳ የሌለን ክፉዎች ነን። በርግጥም እግዚአብሔርን እና የሰው ልጆችን መውደድ ካልቻልን በዓሉን ማክበር አይገባንም።›› ብሎ አቀረቀረ።

ተሰማ በበኩሉ ‹‹እኔ ግን እናንተ እንደምትሉት አይመስለኝም። ለሰው ልጅ ፍቅር የሚሰጡ እና በጎ ነገር የሚያደርጉ ሞልተዋል።›› ሲል ዘውዴ ግን ከተሰማ ፍፁም በተቃረነ መልኩ፤ ‹‹ ተው እንጂ ተሴ ከሚሊየን አንዱ የሚያደርገውን በመጥቀስ መገለጫችን ነው ማለት አይቻልም። ብዙሃኑን አስበህ መናገር ይሻላል። እኛ እኮ እግዚአብሔርን እንወዳለን እያልን የአምላክን ልደት ለማክበር የምንሞክር ደፋሮች ብንሆንም፤ እውነታው ግን ደካሞች ላይ የምንበረታ ጨካኞች፤ የሞተን ሰው እንኳ ይቅር ለማለት የምንቸገር ግብዞች፤ አልፈን ተርፈን የሞተን የምንሰቅል አረመኔዎች ነን። ›› እያለ እየተንገሸገሸ እየተንቀጠቀጠ ሲናገር፤ ገብረየስ ፊቱን ቅጭም አድርጎ ‹‹ ብዙሃኑን መኮነን እንኳ ትክክል አይደለም። ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ደካማን የማገዝ ባህል ያለው ለሴት እና ለሕፃን የሚሳሳ፤ ዕድሜው የገፋ ሰውን አብዝቶ የሚያከብር መሆኑን መካድ አትችልም።›› አለው።

ተሰማ ገብረየስን በመደገፍ፤ ‹‹ማየት የምንችለው ማየት የምንፈልገውን ነው። ዘውዱ ሁልጊዜም የሚታዩት አጥፊ የሆኑ ክፉ ሰዎች ብቻ ናቸው። ደግ ሰዎች ሲኖሩ አውቆ ሳይሆን ሳያውቅ ሳያይ ያልፋቸዋል። የሚሠሩትን አያስተውልም። ክፉ ሰዎችን ደግሞ ተከታትሎ ያያቸዋል። ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ ክፉ ይመስለዋል። ሰው ክፉ ብቻ ሳይሆን፤ ደግም ነው። ለሰው ልጅ በብዙ መልኩ ክብር ያለው ሰው እንዳለ ሁሉ በብዙ መልኩ ሰዎችን በማዋረድ ሥነልቦና ውስጥ ያደገ ያንንም እየተገበረ የሚኖር እንዳለ አይካድም።

ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ጥሩ ለሰዎች ክብር የመስጠት ይቅር የማለት ባህል አለ። እንደውም ከእነ አባባሉ በሽማግሌ የታረቀ በፀሐይ የደረቀ ይባላል። ይህ የሚባልበት ምክንያት ሽማግሌ ያስማማው ዕርቅ የሠመረ ይሆናል በሚል እምነት ነው። ሰው ይህንን የሚለው ለታላላቅ ሽማግሌዎች አክብሮት እና ፍቅር ስላለው ነው። ደግሞም ጠብ ቢኖርም በይቅርታ በፍቅር ይተካል። ስለዚህ ሙሉ ለሙሉ ፍቅር የለም። የገና የአምላክ ፍቅር የተገለጠበት በዓልም መከበር የለበትም ማለት አይገባም።›› ሲል ተናገረ።

ዘውዱ ግን ሃሳቡ ፍፁም ከተሰማ የተቃረነ ነው። ‹‹በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ አሁን የክርስቶስ መወለድን ለማክበር የሚያበቃ ፍቅር የለም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ፍቅር ሳይኖር በዓል አከብራለሁ ማለት ራስን መሸንገል ነው። በዓል የሚያስደስተው ከተግባር ጋር ሲጣመር ነው። የኢትዮጵያ በዓል ግን በተለይ አሁን አሁን ከተግባር ጋር የተጣመረ ሳይሆን የተቃረነ ነው። ግፍ እየፈፀሙ በዓል መከበር የለበትም።›› ሲል ያመነበትን ተናገረ። አንድ ወንድም ቢታሠር አንድ ቀን ለመጎብኘት ወደ እስር ቤት ለመሔድ አንሞክርም። የተወሰነ ሰው ግን ይህንን ሊያደርግ ይችል ይሆናል። ይሆናል ካለ በኋላ፤ ስሜቱን በማረጋጋት አንድ ታሪክ ሊነግራቸው ወደደ።

ከብዙ ዓመታት በፊት ስለተከሰተና አንድ የጎረቤት አርሶ አደርን ስለሚመለከት ጉዳይ መግለፅ ጀመረ። ጎረቤታሞች ብቻ ሳይሆኑ ጥብቅ ጓደኛሞች የነበሩት ወንዶች ሚስቶቻቸው በአብዛኛው ስምምነት ስላልነበራቸው በእነርሱ መጣላት ይጨነቁ ነበር። ‹ኧረ እባካችሁ ለምን ፍቅር አይኖራችሁም ? › እያሉ ይወቅሷቸው ነበር። አንድ ቀን አንዱ አርሶ አደር በጤፍ ማሳ የጎመራው የጓደኛው ይዞታ ላይ ከብት ሲገባ አይቶ ዝም ይላል። የጓደኛው ሚስት ይህንን አይታ ትታዘባለች። በባሏ ይዞታ ውስጥ ያለውን ከብት የባሏ ጓደኛ እንዲሁም ጎረቤት የሆነው ሰው ለማውጣት አለመፈለጉ የደረሰው ጤፍ መርገፉ እና በዚህም ምክንያት ለረሃብ የሚጋለጡበትን ሁኔታ መከላከል እየቻለ የባሏ ወዳጅ ይህን አለመሞከሩ እጅግ አበሳጫት። ለራሷ ‹እነርሱ ፍቅር ሳይኖራቸው ፍቅር ይኑራችሁ ይሉናል።› ብላ ታዝባ ዝም አለች።

ያየችውን ለባሏ ለመንገር አሰበችና ተወችው። ባሏ በበኩሉ በዛው ሰሞን ከአካባቢው ርቆ ሔዱ ሲመለስ ለጓደኛው ስጦታ ይዞ መጣ። ለመስጠት ሲነሳ ግን ሚስቱ አልፈቀደችለትም። ባል የሚስትን ምክንያት ባያውቅም ነገር ግን ገፍቷት መሔድ አልወደደምና ስጦታ መስጠቱን ተወው። በጓደኛው ማሳ ላይ ከብት ሲገባ ተመልክቶ ያልተከላከለው አጥፊው አርሶ አደር፤ ውሎ አድሮ በድርጊቱ ተፀፀተ። ብዙም ሳይቆይ ይቅርታ ለመጠየቅ ወሰነና ወደ ጎረቤቱ ቤት አመራ። እንደደረሰ ጓደኛው እግር ላይ ወድቆ ‹ ተጸጽቻለሁ፤ አጥፍቻለሁ ይቅር በለኝ› ብሎ ተማፀነ። ጓደኛው ግን ጥፋቱን አላወቀምና ይቅር ብዬሃለሁ ተነስ ብሎ አስነሳው። ካስነሳው በኋላ ምን እንደፈፀመ ሲጠይቀው የፈፀመውን ስህተት ነገረው።

እኔ በርሃብ እንድሰቃይ የፈረደብኝ ሰው በፍፁም ይቅርታ አይገባውም ሲል አሰበ። ‹ፍፁም ይቅር አልልህም› አለ። ያንን ያደረገው ሰው አሁን ሞቷል። ይቅርታ አላደርግም ያለው ሰው አሁንም በሕይወት አለ። አሁንም ለሞተው ጓደኛው ይቅርታ እንዳላደረገለት በዚህም እንደማይፀፀት ይናገራል። እኛ ጥሩ ብንመስልም ክፋታችን ይሔን ያህል ነው። ተራውን ነገር ይቅር ለማለት የሚያዳግተን ነን። ይሔ አርሶ አደር ቀድሞም ቢሆን ሲያስመስል እንጂ ለጓደኛው በቂ ፍቅር አልነበረውም። ይህ ተራ ጉዳይ ነው። ተለቅ አድርገን ስናየው ደግሞ ራሳችን የሰው ሕይወት ማጥፋት፤ ወይም የሰው ሕይወት እንዲጠፋ ምክንያት እንሆናለን። አንፀፀትም። ብንፀፀትም ይቅርታ ብንጠይቅም ይቅር የሚለን የለም። በሌላ በኩል የበደሉንን ይቅር ለማለት ዝግጁ አይደለንም። በዚህ ሁሉ ውስጥ ሆነን የፍቅር በዓልን፤ ዓለምን ለማዳን ሲል የተወለደውን አምላክ ልደቱን እናክብር ማለታችን እኔ እንደሚመስለኝ ማሾፍ ነው።›› በማለት በዓሉን ለማክበር ብቁ ነን ብሎ እንደማያምን ተናገረ።

ተሰማ፤ ‹‹እኔ ግን ሙሉ ለሙሉ እንዲህ ክፉ እና ጨካኝ ነን ለማለት እቸገራለሁ። በርግጥ እኛ አምላክ ካሳየው ፍቅር ጋር ሊወዳደር ቀርቶ ሊታሰብ የሚችል ፍቅር አለን የሚል እምነት የለኝም። ነገር ግን ከረጅም ጉዞ እና ድካም በኋላ ሀብት ያፈሩ ሰዎች ሰዎችን ሲረዱ አይተናል። ፋብሪካ አቋቁመው ሠራተኞች ቀጥረው ለሰዎች የሥራ ዕድልን ሲፈጥሩ አስተውለናል። ተስፋ ቆርጠው መታከሚያ አጥተው ሞታቸውን ሲጠባበቁ የነበሩ በሽተኞችን አክመው እና አሳክመው እንዲድኑ ድጋፍ የሚያደርጉ ሰዎች መኖራቸውንም አስተውለናል። በየመንገዱ በፀጥታ ተስፋ ቆርጠው የሚያለቅሱትንም ከበው የሚያናግሩ፤ ያላቸውን ሰጥተው የሚያፅናኑ መኖራቸውንም አንክድም። ይህንን የሚያደርጉ ደግሞ ጥቂት ሳይሆኑ ብዙ ናቸው። ነገር ግን ይህንን ለማየት ክፉ ክፉውን ብቻ ሳይሆን ደግ ደጉንም ለማየት እና ለማዳመጥ መሞከር አለብን። ደግ ደጉ ከታየን ይህንን የፍቅር በዓል ለማክበር ብዙ የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ።›› ሲል በተቃራኒው ያለውን እምነት ተናገረ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ሆሊውድ ወስዶ ወረራ በኢትዮጵያ

ሙሉጌታ ብርሃኑ



ለዚያ ጥቁር ምስጋና ይግባውና ይህን ጽሑፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ አንድ አፍሪካዊ ወጣት ነበር።

ከቀናት በፊት የማኅበራዊ ድረ-ገጽ ትስስር በሆነው ዩቱብ፣ አንድ ጥቁር አፍሪካዊ ወጣት የአንድ የሆሊውድ ፊልምን ምስል እያሳየ ደጋግሞ ኢትዮጵያ . . . አቢሲኒያ እያለ ስሟን ይጠራል። ይህንን ወጣት በስሜታዊነትና በልበ ሙሉነት ሲያወራ ለተመለከተ አንድ ኢትዮጵያዊ የታሪክ ምሁር እንጂ አንድ ጥቁር ዩጋንዳዊ የሚዲያ ዘዋሪ አይመስልም። የሚያወራው ነገር ከጆሮዬ ቀድሞ ልቤን ሰርስሮ የገባ መሰለኝ። ኢንግሊዛዊው ደራሲ ቶልኪን "ሎርድ ኦፍ ዘ ሪንግስ የተሰኘው ፊልም ታሪክ ምናብ የተቀላቀለበት የጥንት የእንግሊዝ ታሪክ ነው ብሎ ነበር፤ ግን ውሸቱን ነው። ቶልኪን ውሸታም ነው፤ ይህ የአቢሲኒያዊያን፤ የአፍሪካዊቷ ሀገር የኢትዮጵያ ታሪክ ነው። . . . ይህን ተመልከቱ . . . ይህ በጥንታዊቷ ሀገር የነበር ነው . . . ይህ ደግሞ አሁንም ያለ . . ." እያለ ወጣቱ ጥቁር ገለጻውን ይቀጥላል። ይበልጥ ቀልቤን እየሳበው መጣ። በጥቂት የነካካቸው ታሪኮች የኛ ስለመሆናቸው ጥርጥር ባይኖረኝም ፊልሙን ለመመልከት ጓጓሁ። ጓጉቼም አልቀረሁ፤ በብዙ ክፍሎች የታጨቀውን ይህን ፊልም በከፊል ተመለከትኩት። ወጣቱ አልተሳሳተም። እንዲያው እሱ ያልጠቀሳቸው በርካታ ነገሮችን ለማስተዋል ቻልኩኝ። የነገሩን ጅራት ይበልጥ ለማዳበር የኛን ሀገር የማህበራዊ ሚዲያ ድረገጾችን ብበረብረም የታሪክ አዋቂ ነን በማለት ታሪክ እያቦኩ፣ እዚህም እዚያም ከሚመርጉ የሚዲያ አብዮተኞች ለበስመአብ ያህል አንድ እንኳን ሳላገኝ ቀረሁ። ከዚያ ይልቅ ወጣቱን ጨምሮ ጥቂት የማይባሉ አፍሪካዊያንና እራሳቸው ነጮቹም በፊልሙ ውስጥ የታሪክ ሽሚያ ስለመካሄዱ ሲቀባበሉት ተመለከትኩ። ልቤን ደስ እንደመሰኘት ነሸጠውና መልሶ የሀፍረት ስሜት ቸለሰብኝ። እራሳችንን ታዘብኩበት። ውስጣዊ ጉዳይ ሲሆን ከሰው ኪስ ወድቆ ቅጭል! ያለችዋን ሳንቲም የኔ ነው፣ የኔ ነው እያልን በመነጣጠቅ ሚዲያውን በአንድ እግሩ የምናቆም እኛ ለዚህ ታላቅ ሀገራዊ ጉዳይ ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ማለታችን አይ ነዶ! . . . የሚያስብል ነው። ይሄኔ ታሪኩ የአንዱ ብሔር ነው ተብሎ ቢሆንማ . . . ብዬ ለማሰብ ሞከርኩና አለማሰብ ይሻላል ብዬ ተውኩት።

'ሎርድ ኦፍ ዘ ሪንግስ' አስቀድሞ መጽሐፍ የነበረ ሲሆን ከፍተኛ ተወዳጅነትና ተነባቢነትን ከማግኘቱ የተነሳ ወደ ፊልም ስክሪፕት ተቀይሮ የተሠራ የሆሊውድ ፊልም ነው። ጸሐፊው ኢንግሊዛዊው ደራሲ ቶልኪን ነው። ታሪኩ ለእንግሊዝ መረቅ፤ ለሆሊውድ ደግሞ ሙዳ ሥጋ ሆኖላቸዋል። ከፊልሙ በተገኘው ከፍተኛ ገቢ ሆሊውድ የገንዘብ ጎተራውን ሞላበት። የዝና ገመዱንም ይበልጥ ዘለለበት። በተለያዩ ሽልማቶችም ተንበሸበሸ። በማን? ያው በኛው ታሪክ። እንግሊዝም በብዙዎች ዘንድ የምትታወቅበት አንድ ባህሪ አላት። እንኳንስ እንዲህ ዓይነቱን የታሪክ አልማዝ ቀርቶ ያየች የተመለከተችውን ሁሉ የመሰብሰብ አባዜ የተጸናወታት መሆኗ ነው። ሰብስባም አታበቃ ድንገት መልሺልኝ ላላት፣ "ዓይኔን ግንባር ያድርገው፤ የኔ ነው" በማለት ምላ፣ ተገዝታ ትክዳለች። በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ የቤተ መንግሥቱን ጓዳ ጎድጓዳ ሳይቀር በርብራ የዘረፈቻቸው ቁጥር ሥፍር የሌላቸው መጻሕፍትን ጨምሮ በየዘመናቱ የምትሰልባቸውን ልዩ ልዩ ቅርሶችን አሁንም የሙጢኝ ብላ አልሰጥም ማለቷ ለዚህ ማስረገጫ ነው። እንኳንስ የምድራችንን የእውቀት በር መግቢያ የያዙትን ቅርሳ ቅርሶች ቀርቶና ከራስ ላይ ፀጉር ሳይቀር ቆርጣ መውሰዷ፤ በእኛ ላይ እጅጉን ከመጎምዠቷ የተነሳ ልቧ በዚህ መታወሩን የሚያሳይ ነው። የተጸናወታት በሰው ወርቅ የመድመቅ አባዜ አለቅ ቢላት ከኛ በሰበሰበቻቸው ቅርሶች ሙዚየሞችን ከፍታ ከተለያዩ ዓለማት የሚመጡ ጎብኚዎቿንና እኛኑ ታስጎበኘናለች። እንግዲህ ደርሳችሁ ባትነኩትም ቢያንስ እዩት ማለቷ ነው። ደራሲው ቶልኪንም የአብራኳ ክፋይ ነውና ሽንጡን ገትሮ ታሪኩ የእንግሊዝ እንጂ የማንም አይደለም ማለቱ ከእርሷው እግር ስር ቁጭ ብሎ የተማረው ነው። የእንግሊዝንና የመጽሐፉን ጉዳይ በአንድ እግር እረግጠን እንለፈውና ነገር ግን ፊልሙ እንዴት በኛ የታሪክ አጥር እንደዘለለ እንመልከት።

በመጀመሪያ፤ ግልጽና ቀላል ወደሆኑትና ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንዲህ አይቶ ሊገነዘባቸው ወደሚችላቸው ነጥቦች እንሂድ። በዚህ ጉዟችንም በፊልሙ ውስጥ የተጠቀሱትን የቦታ ስያሜዎችን እናገኛለን። በ'ሎርድ ኦፍ ዘ ሪንግስ' የተካተተው አንደኛው ከተማ 'ጎንዶር' የሚል ስያሜ ያለው ነው። በገጽታ አሳሳሉ ከነመልክና ወዘናው ጎንደርን ይመስላል። 2ኛ. 'ሐራድ'፤ በኢትዮጵያ. . . ሐረር 3ኛ.'ባራዱር'፤ የኛው ባሕርዳር . . . 4ኛ.'ሮሐን'፤... ሮሐ ወይንም ላሊበላ 5ኛ.'ጎርጎሮት'፤ . . . ጎርጎራ 6ኛ.'ሊበነን'፤ . . . ሊባኖስ ወይም ደብረ ሊባኖስ ናቸው። ስማቸው ብቻም ሳይሆን ሁለመናቸው ከኛ ከተሞች ጋር ልክክ ብሎ መግጠሙ አጋጣሚ ከተባለ የሚያስነውር ነው።

'ጎንዶር' በሲንዳሪያን ቋንቋ የድንጋይ መሬት እንደማለት ሲሆን፤ ከተማው የተዋቀረውም በድንጋይ ነው። ቤተመንግሥቱ ሳይቀር የጎንደርን የመሰለ ነው። አለፍ ሲል አንዳንድ ቅርጻቅርጾችንም እናስተውላለን። አጼ ፋሲለደስ ጎንደርን ከመመስረታቸው አስቀድሞ በድንጋይ የተሞላች፤ በከርሰ ምድሯም ውድ ማዕድናትን የተሸከመች ከተማን አምላክ እንዳሳያቸው በነገሥተ ጎንደር የብራና መጽሐፍ ላይ ተቀምጧል። ከኛ ከባለቤቶቹ ይልቅ መጻሕፍቱም የሚገኙት እነርሱ ዘንድ በመሆናቸው ከኛ ጋር አንድ ዓይነት ሆኖ የሚታየን የትኛውም ታሪክ ቢኖር አያስገርምም። በ'ጎንዶር' እና ጎንደር መሃከል ተመሳስለው የሚታዩ ሌሎች በርካታ ነገሮችም አሉ። ሰሜናዊቷ የጎንደር ከተማ በሰባት ቁጥር አሐዛዊ ቀመር የተሠራች ናት። 'ጎንዶር'ም እንዲሁ . . . ለምሳሌ አጼ ፋሲለደስ ሰባት የወንዝ ድልድዮችን በዙሪያዋ አሠርተዋል። በመጀመሪያ ያነጹት ሰባት አቢያተ ክርስቲያናትን ነበር። የጎንደር ከተማን ሠርቶ ለመጨረስ ሰባት ዓመታትን ፈጅቷል። ለዚህም ተገንብታ ስታልቅ ለሰባት ቀናት ያህል ነጋሪት እየተጎሠመ ተጨፍሯል። ታዲያ በፊልሙ የምንመለከተው የ'ጎንዶር' ከተማም በሰባት ቁጥር አሐዛዊ ስሌት የቆመ መሆኑን እንመለከታለን። ለከተማውና ለነገሥታቱ እንደ መለያ አሊያም እንደ ባንዲራ የሚያገለግለው ጠፍጣፋ ጦር መሳይ፣ ዙሪያው በሰባት አብረቅራቂ ክዋክብት የተዋቀረ ነው።

ጻጉድ በይ ሀገር" ብለን አለፍ ልንል ስንል ደግሞ የጀንተከልን ዋርካን ዘርፈፍ ብሎ እንደቆመ እንመለከተዋለን። በፊልሙ ውስጥ፤ ይህ ግዙፍ ዋርካ የሚገኘው ከቤተመንግሥቱ ፊት ለፊትና ከዋናው መግቢያ በር ሲሆን በጎንደር ከተማም ይህን እድሜ ጠገብ ዋርካ የምናገኘው ከፋሲለደስ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት መሆኑ ነው።

ከመሬት ገጽታና አቀማመጥ አንጻር ደግሞ በፊልሙ ላይ የሚታየው 'አንገረን ሪቨር' በቀጥታ የአንገረብ ወንዝን መልክ የያዘ ነው። 'ሚስት ማውንቴን' እያሉ የሚጠሩት ከተራራ አናት የሚወጣው እሳታማ ጎሞራ ቅርጽና ባህሪው ከኤርታሌ ጋር ተመሳስሎሽ ያለው ነው። ሌላው 'ማውንት ዱም' ሲሆን ደብረ ዳሞን ወክሎ የተቀመጠ ነው። 'አይዘንጋርድ' በዚህ ፊልም ላይ የነገሥታቱን ገጽታ የሚያሳይ በእጅጉ ወሳኙ ስፍራና ከረዥም የድንጋይ ጡብ የተሠራና የተለያዩ ቅርሶችን የያዘ ስፍራ ነው። ይህ ደግሞ ከዲዛይንና ቅርጹ ጀምሮ በአክሱም ነገሥታት የተሠራውን የአክሱምን ሐውልት ምንነት የያዘ ነው። 'ሎርድ ኦፍ ዘ ሪንግስ'ን ለተመለከተ ለአንድ ታሪክ አዋቂ ኢትዮጵያዊ፤ ከፊልሙ ውስጥ የኛ የሆኑትን ነገሮች አበጥሮ ማውጣት ከጤፍ ክምር ውስጥ አሸዋ እንደመልቀም ነው። ከዚያ ይልቅ የኛ ያልሆኑትን ነገሮች መለየቱ እምብዛም ጊዜ የማይፈጅ ነገር ነው።

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በኢትዮጵያ የነበሩት የነገሥታት የዘር ሐረግ ወይም ስርወ መንግሥትን ስናይ ሦስት ነበሩ። እነዚህም የአክሱም (የዛግዌ)፣ የላሊበላ (ሮሐ) እና የጎንደር ነገሥታት ናቸው። 'ሎርድ ኦፍ ዘ ሪንግስ' ይህንንም አልተወልንም። እንደዋነኛ የታሪክ መነሻ ጭብጦች የተካተቱት የስርወ መንግሥታቱ አላባዊያን ሦስት ሲሆኑ፤ እነሱም 'ኪንግ ኦፍ አርሎን'፣ 'ኪንግ ኦፍ ሮሐ'፣ እና 'ኪንግ ኦፍ ጎንዶር' ናቸው። ከፊልሙ ውስጥ ከሚገኙ ገቢሮች ከአንደኛው ትንሿ ቆንጠር ስናደርግ፤ . . . በ'ጎንዶር'፤ የኢልሲደር የነገሥታት የዘር ሐረግ ከተቋረጠ በኋላ በመጨረሻ በመጣው አገዛዝ ሕዝቡ ደስተኛ ስላልነበረ የተለያዩ አመጾችን ያስነሳል። በዚህ ጊዜ ጋንዳልፎ ዘ ግሬይ በተባለ ጠቢብ አማካኝነት ሌላ ንጉሥ ተሹሞ ሥርዓቱ ወደ ትክክለኛው የሕዝብ ተወዳጅነት ሲመለስ ይታያል። ይህ ታዲያ በሀገራችን እንዲህ ነው፤ . . . የሰለሞን ነገሥታት የዘር ሐረግ ከተቋረጠ በኋላ የመጣው የዛግዌ ስርወ መንግሥት ላይ ሕዝቡ ደስተኛ አልነበረም። የዚህን ጊዜ አቡነ ተ/ሃይማኖት ተነሥተው ይኩኖ አምላክን በማንገሥ ዙፋኑ ዳግም እንዲጠነክር አደረጉ . . . የጋንዳልፎ ዘ ግሬይና የአቡነ ተ/ሃይማኖት ተመሳሳይ ተግባር በዚህ አያበቃም። በአቡነ ተ/ሃይማኖት ገድል ውስጥ ማርያን የተባሉት አጋንንት ሳቢዎች በእሳቸው አማካኝነት ወደ ጥልቁ የእሳት ባህር እንደገቡና እንደወደቁ ተጽፏል። የፊልሙ ግሬይም 'ባህሮግ' የተባለውን የጥንቱ ዓለም አጋንንትን ወደ ጥልቁ የእሳት ባህር ሲከተው ያሳያል . . . አጃኢብ ነው! በ'ሎርድ ኦፍ ዘ ሪንግ' የአቢሲኒያ ምድር ያልሆኑ ነገሮች ቢኖሩ፤ ተዋንያኑ ብቻ ናቸው ቢባል ማጋነንም ሆነ ቅጥፈት አይደለም። በአክሱም ውስጥ ኢዛናና ሲዛና የተባሉ ሁለት ወንድማማቾች ስለመንገሣቸው አይዘነጋም፤ ፊልሙም አልዘነጋውም፤ ኢሲልደርና አርኖን በሚል።

ከሥነ ፍጥረትና ስልጣኔ አንጻር ብንመለከት ይህን እናገኛለን። 'ጎለም' በመካከለኛው የምድር ክፍል የሚገኝና በአራት እግር የሚንቀሳቀስ፤ በገጽታውም ሰውን ወደ መምሰል የቀረበ ልዩ የሆነ አፈ ታሪካዊ ፍጡር ተደርጎ ቀርቧል። ይህ ደግሞ በጥንት አባትና እናቶቻችን ዘንድ ጎለም/ጎለምሸት እየተባለ የሚጠራው የክፉ ዛር መንፈስ ስለመሆኑ ከነስያሜው ያመላክተናል።

በፊልሙ ውስጥ '5 ዊዛርድስ' የተባሉ በሰውነት ግዝፈትም ሆነ በእውቀት ከሰው ልጆች ላቅ ያሉና በሰው አምሳል የተቀረጹ አምስት ፍጡራን አሉ። በእውቀት እጅግ የመጠቁ፣ አስተዋዮች፣ አስታራቂና የመምራት ክሂሎታቸው ከፍ ያለ ነው። መነሻቸው ደግሞ ማያ ከሚባሉ ከአነስተኛ ጎሣና የዘር ሐረግ ነው። እናም ማያዊያን በጥንቱ ዓለም የስልጣኔ ማማ የነበሩና በሰሜናዊ ሜክሲኮ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ናቸው። እነዚህ ሕዝቦች ደግሞ ቀደም ሲል በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በዝዋይ ሐይቅ አካባቢ በዌጅ ውስጥ ስለመኖራቸው የራሳቸው የታሪክ ምሁራን በአሥር ጣቶታቸው ፈርመው ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። በዚህ ፊልም ውስጥ አምስቱ ጠቢባን ማያዊያን መሆናቸው፤ እንዲሁም፣ የተገለጹበት መንገድ በቀጥታ በኢትዮጵያ ምድር ወደነበሩት ጠቢባን ይመራናል። ታዲያ ሆሊውድ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪኮች አልዘረፈም? . . . ዘርፏል! ከምትል አንዲት ቃል ጋር እንደ ግል ጠባቂ በቆመ ቃለ አጋኖ ብቻ መግለጽ የልብን አያደርስም። "ቃላቶች ያጥሩኛል" ማለትም ይሄኔ ነው። ይህ ፊልም የተጻፈው በአንድ እንግሊዛዊ ሳይሆን፤ ምናልባትም በአንድ ጎበዝ ኢትዮጵያዊ ደራሲ መስሎ ቢሰማንም አይፈርድብንም። እነዚህ ታሪኮች የተጻፉባቸው የብራና መጻሕፍት አሁንም ድረስ በነጮቹ በተለይም በእንግሊዝ እጅ መሆናቸው የሚያንገበግብ ነው። በነገራችን ከኢትዮጵያ የታሪክ ማህደር ተሰርቆ የተሠራው 'ሎርድስ ኦፍ ዘ ሪነግ' ብቻ አይደለም። "አቫተር"ን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ፊልሞችም አሉ። በፊልም ውስጥም ሆነ በገሀዱ ዓለም የመሰወር ጥበብ ምን እንደሆን ሳይታወቅ በፊት የኛ የጥንት አባቶች ግን እጸ መሰውርን ተጠቅመው እንኳንስ ሰውንና ግዙፎቹን ከተሞችንም ይሰውሩበት ነበር። እንግዲህ "ያልተነጠቅነው ጥበብ፤ ያልተለቀመብን እውቀት ምን አለ?" ከተባለ መልሱ ከ"ምንም" በስተቀር ሌላ ሊሆን አይችልም።

ዛሬ ላይ፤ ጀርመኖቹ በግዕዝ ቋንቋ ለመግባባት የቀራቸው ጥቂት ነው። በሀገራቸው ግዕዝን የሚያስተምሩ ዩኒቨርሲቲዎችንና ኮሌጆችን ከፍተው በማስተማርና በማስፋፈት ላይ ይገኛሉ። ባለቤቶቹ የሆነን እኛስ? እኛማ የእነርሱን የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት ቤቶችን የመከፈት ዜና በኩራት እንደጀብዱ እያወራን አለን። አናሳዝንም? ኸረ በጣም! . . . እንዲያውም ለገባንስ "እናሳፍራለን" ማለቱ ይቀላል። ህልም ለማየት የተሳነን ህልም ፈቺዎች . . . በውሃ ጥም የምናልቅ የዓባይ ልጆች . . . መቼ ይሆን ለራሳችን የምንሆነው? የአባቶቻችንን ታሪክ መድገሙ ቀርቶ ታሪክን መያዙ እንዴት ይሳነን? ሀገርን አይደለም መላውን ዓለምን የሚቀይር ምስጢራዊ ሀብቶችን በእጃችን ይዘን፤ እኛ ግን በረሀብ እየተቆላን ለእነርሱ ማዘን ምን የሚሉት አዚም ይሆን . . . የግዕዝ ቋንቋን በሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ በማካተት ወደኋላ ዞረን ከዚህ የእውቀት ባህር ልንጠልቅ ይገባል። ወተቷን ለመጠጣት ላሟን መቀለብ የግድ ነውና። ቋንቋው ለአንደበታቸው ስለሚጣፍጥ ሳይሆን የሚጣፍጠውን ወተት የሚያገኙበት የላሟ አራት ጡቶች ግዕዝ በመሆኑ ነው። ዜጎቻቸውን በማስተማር የሀገራቸውን ሁለተኛና ሦስተኛ ቋንቋ ማድረግ አላማቸው ነው። እንግዲህ በዚህ ከቀጠልን እነርሱ በግዕዝ ሲግባቡ ምን አልከኝ? . . . እያልን በገዛ ቋንቋችን ለጆሮ ባዳ ሆነን መደናቆራችን የማይቀር ነው። በኛ የታሪክና የቅርስ እርሾ፤ እነርሱ ፊልም መስራታቸው የልብ ኩራት እንዲሰማን የሚያደርግ ቢሆንም የኛ ስለመሆኑ እውቅና ሳይሰጡ በድፍረት ክደው ቁጭ ማለታቸው ግን ቅስም የሚሰብር ነው። የኛ ስለመሆኑ የምናውቀውም እኛ ብቻ ነን። "በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደሰ" ሆነና በኛ የታሪክ ላምባ የሚበራው የእንግሊዝ ቤት ነው። በኛ የሀብትና ቅርስ እንጀራ የሚሞላውም የሆሊውድ ሆድ ነው። ከብዙ ማዛጋት የቀረችንን ጉልበት አሟጠን ዛሬም በዓለም አደባባይ ብንጮህ ምናልባትም አልረፈደብን ይሆናል። የፊልም ኢንዱስትሪያችን ንቃት ህሊና እነዚህን በመሳሰሉና ባልተነኩ ታሪክና ቅርሶቻችን የተቃኘ መሆን አለበት። ጥያቄው መሆን ያለበት "ሆሊውድ ለምን ሠራው?" ሳይሆን "እኛ ለምን አልሠራነውም?" ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ግጭት መፍቻዎችን ለሀገራዊ ሠላም

**አስናቀ ፀጋዬ**

በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ከዘመናዊው የዳኝነት ሥርዓት ጋር ባልተናነሰ መልኩ ማኅበረሰቡ ለዘመናት ሲጠቀምባቸው ቆይቷል፤ አሁንም እየተጠቀመባቸው ይገኛል:: በእነዚህ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች አማካኝነት ማኅበረሰቡ ፍትሕ አግኝቷል፤ እያገኘም ነው:: አሁን ላይ በተለያዩ ምክንያቶች በሀገሪቱ ለተከሰቱ ግጭቶች ማኅበረሰቡ በሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የመዳኘት ፍላጎት እንዳለው ጥናቶች ያሳያሉ:: በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች ትልቅ ድርሻ እንዳላቸውና እነርሱን አጎልብቶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ ተነግሯል::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ተመራማሪና መምህር ደሳለኝ አምሳሉ(ዶ/ር) እንደሚናገሩት የሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች ውጤታቸው ከፍ የሚልበት ዓውድ አለ:: በተለይ ግጭቶቹ አካባቢያዊ፣ ሀብትን መሠረት ያደረጉና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሌለባቸው ከሆኑ መፍትሔ ሊያመጡ ይችላሉ:: ከዚህ ባለፈ ግን ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች አሁን ባሉበት ሁኔታ በአሠራር፣ በሕግና በሌሎች መንገዶች ሳይጠናከሩ ሀገራዊ የሆኑ ችግሮችን ለብቻቸው ሊፈቱ አይችሉም:: የራሳቸውን አስተዋፅዖ ግን ሊያበረክቱ ይችላሉ::

ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች አሁን ባለው ሁኔታ ለብቻቸው ለሀገራዊ ችግሮች መፍትሔ ሊያመጡ የማይችሉባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ በበርካታ አካላት የበርካታ ፍላጎቶች መኖር፣ የተለያዩ የታሪክና የፖለቲካ ትርክቶች መንሰራፋት፣ የጉዳዮች ባለቤትና ተዋንያን መብዛት፣ በሀብት ክፍፍል ላይ የተለያየ አቋም መያዝ፣ በውስብስብና ታላላቅ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም አለመኖርና ሌሎችም ናቸው::

በሀገሪቱ በርካታ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች ቢኖሩም የግጭት መፍቻ መንገዶቹ እንደ የአካባቢዎቹ ሁኔታና እንደ ሕዝቡ ፍላጎት የሚለያዩ እንደ መሆናቸው፤ እንዲሁም አንዱ የግጭት መፍቻ መንገድ በሌላው አካባቢ ሊሠራ የማይችልበት ሁኔታ በመኖሩ ሁሉም የግጭት መፍቻ መንገዶች ለሀገራዊ ችግር መፍትሔነት ሊውሉ አይችሉም:: ግን ደግሞ ለመፍትሔው የየራሳቸው አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል::

> **ሀገራዊ ችግሮቹ** የታሪክ፣ የድህነት፣ የሥልጣን ክፍፍል፣ ያልታወቀና የማንነት፣ የክልልነት፣ የፖለቲካና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ

ሀገራዊ ችግሮችን ለመፍታትና በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ለማድረግ ሀገር በቀል ግጭቶችን መጠቀም ይቻላል:: ይህን ማድረግ የሚቻለው ግን የግጭት መፍቻ ዘዴዎቹን ለአካባቢያዊ ችግር መፍቻ መጠቀም ሲቻል ነው:: አካባቢያዊ ችግሮች ሲፈቱ ሀገራዊ ችግሮችን በሌላ መንገድ ለመፍታት ያስችላል::

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ሀገር በቀል ግጭት መፍቻ መንገዶችን ማሳደግ ይቻላል:: በሀገሪቱ ካሉ ከመቶ በላይ የሚጠጉ የግጭት መፍቻ መንገዶችን በማሳደግ ሀገራዊ ግጭቶችን መፍታትና ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ይቻላል:: እነዚህ የግጭት መፍቻ መንገዶች ምንም እንኳን አተገባበራቸውና አካባቢያዊ ዓውዳቸው የሚለያይ ቢሆንም የጋራ የሚያደርጋቸው እሳቤና ግብ አለ:: ይኸውም ሰላም፣ መከባበር፣ አብሮ መኖር ..... እና የመሳሰሉት ናቸው::

ስለዚህ ሀገር በቀል ግጭት መፍቻ መንገዶች የአተገባበራቸው ልዩነት እንዳለ ሆኖ የጋራ የሚያደርጋቸውን ነገር በማሳደግና ወደ ላይ በማምጣት ሀገራዊ የሆኑ፤ ነገር ግን የኢትዮጵያን የባሕል እሴት የጠበቁ ግጭት መፍቻ ሥርዓቶችን መገንባት ይቻላል:: በእነዚሁ የግጭት መፍቻ መንገዶችም ሀገራዊ ችግሮችን መፍታት ይቻላል:: ሚናቸውም ከፍ ይላል:: ይሁንና ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች በሚፈለገው ደረጃ አላደጉም::

ደሳለኝ (ዶ/ር) እንደሚያብራሩት ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች ሁሉንም ሀገራዊ ጉዳዮች ይፈታሉ ማለት አይደለም:: ነገር ግን፣ መፍታት የሚችሏቸውን ችግሮች እንዲፈቱ እድል መስጠት ያስፈልጋል:: ማሳደግ ያስፈልጋል:: በዚህ ላይም ሰፊ ሥራ መሥራት ይገባል:: ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ችግር እንድትወጣና ሰላም እንዲረጋገጥ ሀገር በቀል የግጭት ሥርዓቶችን አሳድጎ ጥቅም ላይ ከማዋል በዘለለ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ድረስ ያሉ የመፍትሔ እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል::

ሀገራዊ ችግሮቹ የታሪክ፣ የድህነት፣ የሥልጣን ክፍፍል፣ ያልታወቀና የማንነት፣ የክልልነት፣ የፖለቲካና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህ ችግሮች በሕግ ውስጥም፤ በአተገባበር ላይም ያሉ ናቸው:: ለአብነትም የማንነትና ያልታወቀ ጥያቄን በተመለከተ በተቀመጠ መስፈርት መሠረት ሕገ መንግሥቱ ይፈቅዳል:: በተመሳሳይ ክልል ለመጠየቅ ወይም ደግሞ ከቀበሌ ወደ ወረዳ ከፍ ለማለት፣ ወረዳ ያለው ዞን ለመጠየቅ፣ ዞን ያለው ክልል ለመጠየቅ፣ ክልል ያለው ሀገር ለመሆን ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው በሕጉ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ ቀላል ነው::

ስለዚህ አሁን ያለውን ሀገራዊ ችግር ለመፍታትና በዋናነት በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ለማድረግ በሕጉ በኩል ያሉ አሠራሮችን ማስተካከል ያስፈልጋል:: በአተገባበር በኩልም ቢሆን ‹‹እኔ ልብላ፣ እኔ ልኑር፣ እኔ ልሰማ፣ እኔ ልደመጥ›› የሚለውን ሀሳብ በመተው አብረን እንኑር፣ አብረን እንሥራ፣ አብረን እንለወጥ፣ አብረን እንብላ፣ አብረን እንደመጥ›› የሚሉትን እሳቤዎች ማስቀጠል ያስፈልጋል:: ይህም ማለት ሙስና፣ ብልሹ አሠራር፣ የአንድ ብሔር የበላይነትና ሌሎችንም ማስወገድ ይገባል:: ከሁሉም በላይ፣ ለሀገራዊ ችግር መፍትሔ ለማምጣት ግን ቁርጠኝነት ያስፈልጋል:: ለዚህም የጋራ መተማመን ሊኖር ይገባል::

በአፈሙዝ ጊዜያዊ ሠላም ሊመጣ ይችላል:: ነገር ግን ዘላቂነት ያለው ሠላም በአፈሙዝ ሊመጣ አይችልም:: ይህም በብዙ ሀገራት ውስጥ ተሞክሮ ውጤቱ ምን እንደሆነ በሚገባ ታይቷል:: ከአፈሙዝ ይልቅ ጠረጴዛ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ይዞ መምጣት ይችላል:: ስለዚህ ከዚህ የጠረጴዛ መፍትሔ በዘለለ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶችን በማሳደግና ለሀገራዊ መፍትሔ በመጠቀም የሚፈለገውን ሠላም ማረጋገጥ ይቻላል::

# ዓለም አቀፍ



## ኢራን ከነዳጅ ንግድ 26 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቷን ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኢራን ከነዳጅ ንግድ 26 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቷን ገለጸች፡፡ በነዳጅ ሀብቷ ከዓለም አራተኛ ደረጃ ላይ ያለችው ኢራን በአሜሪካ ማዕቀብ ምክንያት ነዳጅ ለዓለም ገበያ ማቅረብ አልቻለችም።

በነዳጅ ሀብቷ ከዓለም አራተኛ ደረጃ ላይ ያለችው ኢራን ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ወደ ውጪ ሀገራት ከላከችው ነዳጅ 26 ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቷን አስታውቃለች፡፡

የሀገሪቱ ነዳጅ ሚኒስትር ጃቫድ አውጂ እንዳሉት የኢራን ወጪ ንግድ ገቢ የሰባት በመቶ እድገት ማስመዝገቡን ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ ሀገሪቱ እስከ መጭው መጋቢት ወር ድረስ ከወጪ ንግድ 116 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት አቅዳለች፡፡

ኢራን ከአሜሪካ ጋር ባላት የዲፕሎማሲ መሻከር ምክንያት ማዕቀብ የተጣለባት ሲሆን ይህም ነዳጅን ጨምሮ ምርቶቿን ለዓለም ገበያ በቀላሉ ማቅረብ አልቻለችም፡፡

ቻይና እና ሌሎች የእስያ ሀገራት ዋነኛ የንግድ አጋሯ ሲሆኑ ነዳጇን ከዓለም ገበያ ዝቅ ባለ ዋጋ ለመሸጥ እንደተገደደችም ተገልጿል፡፡

ዓለም አቀፉ የነዳጅ ላኪ ሀገራት ባወጣው መረጃ መሠረት ቬንዙዌላ ባላት ነዳጅ ሀብት የዓለማችን ቀዳሚ የነዳጅ ሀብታም ሀገር ስትሆን ሳዑዲ ዓረቢያ እና ካናዳ ደግሞ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ሀገራት ናቸው፡፡

ኢራን፣ ኢራቅ እና ኩዌት ደግሞ በቅደም ተከተላቸው መሠረት ከአራተኛ እስከ ስድስተኛ ደረጃ ያለውን ደረጃ ይዘዋል፡፡

በነዳጅ ሀብቷ 10 ደረጃ ላይ የምትገኘው አሜሪካ ከ2018 ጀምሮ የዓለማችን ቀዳሚዋ ነዳጅ አምራች ሀገር ስትሆን በ2022 ላይ ብቻ በየቀኑ በአማካኝ 18 ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ አምርታ ለገበያ አቅርባለች፡፡

ሳዑዲ አረቢያ በ2022 ዓመት ብቻ 311 ቢሊዮን ዶላር ከነዳጅ ሽያጭ ገቢ ማግኘቷ ተገልጿል።

## የአሜሪካ ብሔራዊ እዳ መጠን 34 ትሪሊዮን ዶላር ደረሰ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የአሜሪካ ብሔራዊ እዳ መጠን 34 ትሪሊዮን ዶላር አለፈ:: የሀገሪቱ ብድር ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ የ2 ነጥብ 6 ትሪሊዮን ዶላር ጭማሪ አድርጓል::

የዓለማችን ልዕለ ኃያል ሀገር አሜሪካ የእዳ መጠኗ ከ34 ትሪሊዮን ማለፉን የሀገሪቱ ግምጃ ቤት በድረ ገጹ አስታውቋል።

የሀገሪቱ የእዳ መጠን በአሜሪካ ታሪክ ከፍተኛው እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን የዋጋ ግሽበት መፈጠሩ፣ ለዩክሬን እና እስራኤል የተሰጠው እርዳታ በየጊዜው መጨመር የመንግሥት የሚበደረውን የገንዘብ መጠን እንዲጨምር አድርጓል ተብሏል።

የአሜሪካ መንግሥት እዳ መጠን ባሳለፍነው ጥር ላይ 31 ትሪሊዮን ደርሶ የነበረ ሲሆን ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ተጨማሪ ሁለት ነጥብ ስድስት ትሪሊዮን ዶላር ተጨማሪ ብድር መበደሩ ተገልጿል።

ለዩክሬን እና እስራኤል የጦር መሣሪያ እና የገንዘብ ድጋፍ ይደረግ አይደረግ በሚል የሀገሪቱ ሕግ አውጪ ምክር ቤት አባላት ከስምምነት ላይ አለመድረሳቸው ይታወሳል::

ከዚህ በፊት በተለይም የሪፐብሊካን ፓርቲ ተወካዮች በስፋት ይነገር የነበረው የዩክሬን ጦር መሣሪያ ድጋፍ ይቁም የሚለውን ሀሳብ ዲሞክራቶችም እየተቀበሉት ይገኛሉ ተብሏል::

አለመስማማቱን ተከትሎም ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን መንግሥታቸው እንዳይዘጋ በሚል ለቁልፍ ተቋማት እና ሥራዎች ከሚደረግ ወጪ በስተቀር አዲስ በጀት እንዳይፀድቅ ከሪፐብሊካን ተወካዮች ጋር ተስማምተዋል::

ዩክሬን በበኩሏ ከአሜሪካ ተጨማሪ ገንዘብ እና ጦር መሣሪያ እንዲሰጣቸው በመወትወት ላይ ሲሆኑ ሀገራቸው በሩሲያ ከተሸነፈች ሽንፈቱ ከኪየቭ በተጨማሪ የኔቶም ይሆናል ብለዋል::

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዘለንስኪ እ.አ.አ. 2014 ወደ ሩሲያ የተቀላቀለችው ክሪሚያን በተያዘው 2024 ዓመት ከሩሲያ እንደሚነጥሉ በአዲስ ዓመት ንግግራቸው ላይ ቃል ገብተዋል::

ለዚህ እቅዳቸውም ጀርመን የረጅም ርቀት ሚሳኤል ድጋፍ እንድታደርግላት ፕሬዚዳንቱ የጠየቁ ቢሆንም ጀርመን ጥያቄውን ውድቅ አድርጋለች::

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## "ቤት ለእንቦሳ፣ እንቦሳ እሰር፤"

ባለፈው ሰኞ ብሪክስ ፕላስ በኦፊሴል "ቤት ለእንቦሳ፣" ብሎ በእንግድነት ወደ ሀገራችን ገብቷል። እኛም "እንቦሳ እሰር፤" ብለን ተቀብለነዋል። በእንግዳ ተቀባይነታችን የተመሠከረልን፤ እንኳን ሰው ወፍ የምናላምድ ነን። መኙታ ለቀን፣ እግር አጥበን የምናስተናግድ አብርሃማዊ/ኢብራሒማዊ። የአብርሃም እንግዳን ተቀብለን ቤት ያፈራውን አቅርበን በማስተናገዳችን በረከት እናገኛለን።

ብሪክስ ፕላስን በመቀበላችንም ንግድን እናሰፋለን፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን እንስባለን፣ መሠረተ ልማትን እናስፋፋለን፣ የቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር እናደርጋለን፣ ፖለቲካዊ ጫና ለመፍጠር ሌላ የመደራደር አቅም እናገኛለን፣ ኢኮኖሚያዊ ትብብርን እናሳድጋለን። ለዚህ ግን ቤታችንን ማሰናዳት፤ የቤት ሥራችንን አበክረን መሥራት ይጠበቅብናል።

ሀገራችንን ለዓለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ ከሁሉም በፊት የራቀንን ሰላም ማስፈን አለብን። በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች የሚካሄዱ ጦርነቶች በድርድር በንግግር መቋጨት፤ የዴሞክራሲ ተቋማትን ማጎልበት፤ በመንግሥት አካላት ማለትም በሕግ አውጭው፣ ተርጓሚውና አስፈጻሚው መካከል መደበላለቅን ማስወገድ፤ በሂደት በማንነት ላይ ከተመሠረተ ፖለቲካ መውጣት ያስፈልጋል።

የፕሪቶሪያውን ስምምነት መተግበር ማጽናትና ማዝለቅ፤ እዚህም እዚያም የሚታዩ ግጭቶችን ቀድሞ መከላከል፤ ከተከሰቱም ፈጥኖ መቆጣጠር፤ አገልግሎት አሰጣጣችን ፈጣንና ቀልጣፋ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፤ የሕግ የበላይነትን ማስፈን፤ የገነገነውን ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ማስወገድ ይጠበቃል።

የዋጋ ግሽበቱንና እሱን ተከትሎ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት መቆጣጠር፤ የውጭ ምንዛሪ ችግርን መቅረፍ፤ የተፈጥሮ ሀብት ብሔርተኝነትን natural resource nationalism ማስወገድ፤ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማዘጋጀት፤ ለኢንቨስተሩ ማበረታቻዎችን ማቅረብ፤ የኢንዱስትሪ ሰላሙ አስተማማኝ መሆኑን ዋስትና መስጠት፤ ወዘተረፈ ማድረግ አለብን።

ብሪክስ ፕላስን እንቦሳ እሰር ብለን በተቀበልን ማግስት የባሕር በር ማግኘታችን፤ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ደግሞ የዓለም ንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል ተስፋ መሰነቃችን፤ ታላቁን የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ጨምሮ የሌሎች ታዳሽ ኃይሎች ባለቤት መሆናችን፤ በአፍሪካ 126 ሚሊየን ሕዝብ ያለን ባለ ግዙፍ ገበያ መሆናችን፤ በቀጣናዊ ስትራቴጂካዊ ስፍራ መያዛችን፤ ወዘተረፈ መልካም አጋጣሚ ነው። ለመንደርደሪያ ያህል ይህን ካልሁ ወደ ብሪክስ ፕላስ ታሪካዊ ዳራ፣ ተስፋና ስጋት ላምራ።

የብሪክ/BRIC ስረወ-ምህጻረ ቃልም ሆነ ጽንሰ ሃሳብ የተፈጠረው በጎልድማን ሳክስ የኢኮኖሚ ባለሙያ ጂም ኦኔል በጎርጎሮሳዊያኑ አቆጣጠር 2001 ዓ.ም ሲሆን ፤ ብራዚልን ፣ ራሽያን ፣ ሕንድና ቻይናን ያካተተ የኢኮኖሚያዊ ስብስብ ሃሳብ ነው። ይህ እሳቤ በ2009 ዓ.ም እውን ሆነ ። በዓመቱ 2010 ዓ.ም ደቡብ አፍሪካን አካቶ ብሪክስ ፕላስ/BRICS + ሆነ።

የምዕራባውያን ጉልሃን ወይም ኤሊቶች በስብስቡ የቻይናን የበላይነት ለመግለጽ ብሪክስ ፕላስን ቻይና ሲደመር አራት ወይም China + 4 ይሉታል። በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ በተካሄደው የብሪክስ ፕላስ 15ኛ ጉባኤ ሀገራችንን ጨምሮ ስድስት አዲስ አባላትን ሲጨምር ደግሞ China + 10 ተለዋጭ ስያሜ ሰጥተውታል። ምዕራባውያን እነሱ ቡራኬ ያልሰጡትን ስብስብ እንዲህ በነገር ይሸነቁጡታል። አርጀንቲና በቅርብ ባካሄደችው ምርጫ መሪዋን ከለወጠች በኋላ ግን ብሪክስ ፕላስን የመቀላቀሉ ነገር ይቆየኝ ማለቷ እየተነገረ ነው።

በ"The Ethiopian Economist View" ድረ ገጻቸው ቢዝነስ፣ ኢኮኖሚክስና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በመጻፍ፤ ማህበራዊ ሚዲያውን በተለይ ፌስቡክን ለበጎ አላማ በማዋል የሚታወቁት የኢኮኖሚክስ ባለሙያው አቶ ዋሲሁን በላይ፤ የተጨመሩት 6 አዲስ አባል ሀገራት በጠቅላላ 410 ሚሊየን ሕዝብ ያላቸው በመሆኑ የአባል ሀገራት ሕዝብ ብዛትን ወደ 4.2 ቢሊየን ያደርሱታል።

ነባር አባል ሀገራቱ ያላቸው ጠቅላላ የምርት መጠን (GDP) 26 ትሪሊዮን ዶላር ይደርሳል (ከዓለም ጠቅላላ ምርት መጠን ውስጥ 26 ከመቶ ነው)። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ እስከ ቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ድረስ የነበረው የዓለም ሀገራት በርዕዮተ ዓለም የመቧደን ዓይነት አዝማሚያ ያለው የሚመስል ሆኖ አባል ሀገራቱ በዚህ ወቅት ዓለም በጥቂት ሀገራት የበላይነት መመራቷ ማብቃት አለበት ሲሉ ይሞግታሉ።

አዲሱን አሰላለፍ ወይም BRICS +ን የመቀላቀል ዕድሎችንና ስጋቶችን ማመዛዘን ይገባል:: እድሎች፡- የተሻሻለ የኢኮኖሚ ትብብር ሊፈጠር ይችላል። ለኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ንግድን፣ የውጪ ኢንቨስትመንትን እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማጎልበት ኢኮኖሚያዊ ትብብር እንዲጨምር ያደርግ ይሆናል።

ይህ አጋርነት ቀጣይነት ያለው የኢንዱስትሪ ልማትን ማበረታታት፣ የሥራ እድል መፍጠር እና ፈጠራን ማጎልበት በመጨረሻም የረዥም ጊዜ የኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅዖ ሊያደርግ ይችላል። የመሠረተ ልማት ግንባታ ተስፋዎች ሊኖሩት ይችላል። የቀደሙ የBRICS + አባል ሀገራት (አዲስ የቀላቀሉትንም ጨምሮ) በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ላይ ከፍተኛ እውቀት እና ሀብቶች አሏቸው።

ኢትዮጵያ ህብረቱን በመቀላቀሏ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ጉድለትን ለመፍታት ወሳኝ የሆነውን ሀብት፣ እውቀት እና ልምድ ልታገኝ ትችላለች። ከአዲሱ የBRICS + ልማት ባንክ (New Development Bank) የገንዘብ ድጋፍ በማግኘት የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማፋጠን አስደሳች ዕድል ሊፈጥርላት ይችላል ይሉናል ባለሙያው።

ለምሳሌ፡- የኢትዮጵያ ከዓለም ባንክ ብድር እና ድጋፍ ስታገኝ የኖረች ቢሆንም ጠንካራ ቅድመ ሁኔታ ያለው ብድር ከመሆኑ በተጨማሪ የበለጸጉት ሀገራት ብድሩን እንደ ርዕዮተ ዓለም ማስፈጸሚያ እና ጫና መፍጠሪያ አድርገው ይጠቀማሉ:: ለነገሩ ረዘም ላሉ ዓመታት የብድር ፍላጎቶቿ/እድሎቿ ወደ ቻይና ዞረዋል (የብዙ አፍሪካ ሀገራት አጋርነት ወደ ቻይና የመዞር በቻይና አፍሪካ ጉባኤ እና በዩኤስ አፍሪካ ጉባኤ ላይ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጉዳይ ነው):: ይህን እድል ወደ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለመቀየር ጠንካራ የማምረት አቅም መፍጠር ያስፈልጋል።

ስጋቶች፡-የምዕራባውያን ውጭ ባሉ ሀገሮች ላይ ተመሳሳይ ጥገኝነት መፍጠር አባልነትን ተከትሎ የምዕራብ ሀገራትም ሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት በውሳኔው ደስተኛ ያለመሆን አዝማሚያ ሊኖራቸው ስለሚችል (ቅጣታቸውን ብድር እና ርዳታ ወደ መከልከል የሚያዞሩት ከሆነ) ኢትዮጵያ ወደ ሌሎቹ የBRICS + አባል ሀገራት ይበልጥ ጥገኝነቷን ማዞር ልትጀምር ትችላለች (በተለይ ወደ ቻይና! ይህ አዝማሚያ የBRICS + አባል ከመሆንም በፊት እየታየ የመጣ ነው)::

የንግድ ግንኙነት መዳረሻዎች መለወጥ፡- BRICS +ን መቀላቀል የንግድ መዳረሻዎችን ወደ አባል ሀገራት ገበያዎች አቅጣጫ እንዲቀይር ሊያደርግ ይችላል። ይህ ለረጅም ጊዜ የቆየውን የኢትዮጵያ እና የምዕራባውያን እና የአሜሪካ የንግድ ግንኙነቶችን ሊያደናቅፍ ይችላል:: ነገር ግን ኢትዮጵያ የውጭ ገበያ መዳረሻዎቿን በማስፋት የንግድ ልውውጥ እንዲጨምር እና በነጠላ የንግድ አጋሮች ላይ ያላትን ነባር ጥገኝነት እንዲቀንስ አዳዲስ ዕድሎችን ሊከፍትላትም ይችላል።

የመገለል ስጋት፡- BRICS +ን መቀላቀል እንደ የዓለም ባንክ እና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ካሉ ምዕራባውያን ተቋማት ሊያስገልል እንደሚችል ማሰብ ያሻል። ይሁን እንጂ በBRICS + ውስጥ የተመሰረተው አዲስ የልማት ባንክ (New Development Bank) ያሉ አማራጭ የፋይናንስ ዘዴዎች መፈጠራቸው እነዚህን ስጋቶች ለመፍታት እና ለኢትዮጵያ ለመሠረተ ልማትና ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በጣም አስፈላጊ የሆነውን ካፒታል (የውጭ ምንዛሪ) እንድታገኝ ሊያግዛትም ይችላል።

ከዚህ ቀደም ዩናይትድ ስቴትስ እና አንዳንድ ምዕራባውያን ኃያላን የአፍሪካ ሀገራት ከBRICS + ጋር መስማማታቸው ስጋታቸው መሆኑን ገልጸዋል። የBRICS + ታዋቂነት እያደገ በመምጣቱ ዩናይትድ ስቴትስ በአፍሪካ ላይ ያላት ተጽእኖ እየቀነሰ እንዳይሄድ ትሰጋለች። ስለሆነም አጋርነትን ማጠናከር፣ የርዳታ ፖሊሲዎቻቸውን ማሻሻል ወይም ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ጫና ፈጣሪ ርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ ይሉናል አቶ ዋሲሁን።

የአሜሪካው ኢንቨስትመንት ባንክ ጎልድማን ሳክስ በሚቀጥሉት 50 ዓመታት የብሪክስ ፕላስ አባል ከሆኑ ሀገራት ቻይናና ሕንድ አሜሪካንን ቀድመው እንደ ቅደም ተከተላቸው በኢኮኖሚያቸው ዓለምን ይመራሉ ሲል ይተነብያል። ኢትዮጵያም በ6 ነጥብ 2 ትሪሊየን ዶላር ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት 17ኛ ደረጃ ላይ እንደምትቀመጥ ባንኩ አክሎ ጠቁሟል። ይህን ተስፋ የሰነቀች ሀገር አበክራ ብሪክስ ፕላስን ለመቀላቀል ማመልከቷና ተቀባይነትን ማግኘቷ ተገቢ ውሳኔ ብቻ ሳይሆን አርቆ አስተዋይነት ወይም ስትራቴጂካል ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

የዓለም የንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል ደጅ ስትጠና ሶስት አስርት ዓመታትን ላሳለፈች ሀገር፤ አሜሪካ ኢፍትሐዊ በሆነ አግባብ ከአጎዋ ወይም AGOA/ The African Growth and Opportunity Act/ ማለትም ከሰሃራ በታች ለሚገኙ ሀገራት ምርቶቻቸውን ከቀረጥ ነጻ ለአሜሪካ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሚያስችል ዕድል ለታገደች ሀገር፤ ለሀገር በቀል ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዋ ከዓለም ባንክና ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ልታገኘው የነበረ ከ10 ቢሊየን ዶላር በላይ ድጋፍና ርዳታ በአሜሪካና በምዕራባውያን በመታገዱ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈለች ላለች ሀገር ብሪክስ ፕላስን መቀላቀሏ ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው። ለመሆኑ ይሄ ለብልጽግና ለእድገት ስትራቴጂካዊ መነሻም መውጫም የሆነው ብሪክስ ፕላስ ማን ነው።

"ብሪክስ ፕላስ" ወይም "BRICS +" የሚለው ምህጻረ ቃል በማደግ ላይ ያሉ የአምስት ሀገራትን ስብስብ የሚወክል ሲሆን የየሀገራቱን የመጀመሪያ ሆሄ በመውሰድ የተፈጠረ መጠሪያ ነው። 'B'ን ከBrazil፣ 'R'ን ከRussia፣ 'I'ን ከIndia፣ 'C'ን ከChaina በመጨረሻም 'S'ን ከSouth Africa በመውሰድ "BRICS +" የሚለው ስያሜ ተመሠረተ። መጠሪያው የተፈጠረው በ2001 ዓ.ም ጂም ኦኔል በተባለ የኢኮኖሚክስ ጠበብት ሲሆን እነዚህ ሀገራት በ21ኛው መክዘ በዓለም ኢኮኖሚ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሚሆኑ ተንብዮ ነበር።

ከ22 ዓመታት በኋላ ዛሬ ያረጋገጥነው ትንበያው ጠብ ያላለና ትክክለኛ ሆኖ መሆኑን ነው። የብሪክስ ፕላስ ሀገራት በተለያየ የጂኦግራፊ ክልል የሚገኙ ሲሆኑ፣ የሕዝብ ብዛታቸው ከ3 ቢሊየን በላይ ወይም ከዓለማችን ሕዝብ 40 በመቶውን የያዙ፤ ከዓለማችን መሬት ወይም የብስ 26 በመቶ የሚሸፍኑ፤ ከዓለማችን ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት 23 በመቶ ድርሻ ያላቸው ናቸው ።

የተመሠረተበት ዋና ዓላማ በሀገራቱ መካከል ትብብር ለመፍጠርና ለመመካከር ነው። እርስ በርስ ለመነገድ፣ ኢንቨስት ለማድረግና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማሳለጥ የተቋቋመ ስብስብ ነው። በየጊዜው በመደበኛነት በመሰባሰብ ስለ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ቀጣይነት ስላለው ልማት፣ ስለዓለም አቀፍ አመራርና ጸጥታ ይመክራሉ። ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ።

ብሪክስ ፕላስ ከተቋቋመበት አላማ አንዱ ብሪክስ ፕላስ ባንክ የተሰኘ አዲስ ባንክ ማቋቋም ነው። ባንኩ ለአባል ሀገራቱ ሆነ ለሌሎች ለመሠረተ ልማት ግንባታ እና ቀጣይነት ላላቸው ልማቶች ብድር ያቀርባል። በአሜሪካና በምዕራባውያን ቅድመ ሁኔታዎችና እጅ ጥምዘዛዎች ስር ከወደቁት የዓለም ባንክና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ተጽዕኖ በመላቀቅና አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

ከዚህ በተጨማሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ኢነርጂ፣ ጤናና ትምህርት ላይ በስፋት የመሥራት ዕቅድ አለው። በሀገራቱ መካከል ትብብርንና የልምድ ልውውጥን ለማሳለጥ የጋራ ፎረም መመስረቱን ሰነዶች ያወሳሉ። በአባላቱ መካከል መተባበርና መደጋገፍ እንዳለው ሁሉ ተግዳሮቶችና ልዩነቶችም አሉ።

እያንዳንዱ ሀገር የየራሱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ባህሪ ያለው መሆኑ የመጀመሪያው ተግዳሮት ሲሆን የጋራ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት ወይም የየሀገራቱ ፍላጎት በእኔ እብስ በእኔ እብስ የሚሳሳቡበትና የሚራኮቱበት መድረክ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋትም አለ። ጂኦፖለቲካው ውጥረት፣ የንግድ ግጭቶችና የሚከተሉት የኢኮኖሚ ሥርዓት ለስብስቡ አንድነት ስጋቶች ናቸው።

ያም አለ ይህ ብሪክስ ፕላስ በማደግ ላይ ላሉት 11 ሀገራት ድምጽም መድረክም ነው። ስጋታቸውን የሚያሳስቡበት፣ ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩበት፣ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ተገቢውን ሥፍራና ትኩረት እንዲያገኙ የሚጠይቁበት የጋራ መድረክ ነው።

የብሪክስ ፕላስ አባል ሀገራትን ከፖለቲካ ይልቅ ምጣኔ ሀብት እንዳስተሳሰራቸው ተደጋግሞ ታይቷል። ከሰሞኑ የአባል ሀገራቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በደቡብ አፍሪካ ተገናኝተው ነበር። በዚህ ወቅትም ዓለም በምዕራባዊያን ከሚዘወረው ሥርዓት መውጣት እንዳለባት አንስተዋል።

የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ናሌዲ ፓንዶር፤ ቡድኑ በጂኦፖለቲካ ውጥረት፣ በእኩልነት አለመኖር እና በደኅንነት ስጋት ውስጥ ላለው ዓለም ሃሳብ ይዞ መቅረቡን ገልጸዋል። የሕንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በበኩላቸው ሱብራህማንያም ጃይሻንካር ስብስቡ ዓለም ባለብዙ መልክ ስለሆነች ባረጀው መንገድ አዲሱን አጀንዳ መፈጸም አይቻልም። ከምንጋፈጣቸው ችግሮች አንዱ የምጣኔ ሀብት ጉዳይ ሲሆን ብዙ ሀገራት በጥቂቶች በጎ ፈቃድ እንዲኖሩም ሆነዋል ብለዋል።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት



## ብሔራዊ ቡድኑን ከስደት ለመመለስ ያለመው የባሕርዳር ስታዲየም ማሻሻያ ግንባታ

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ ወንዶች ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን እአአ ከ2014 አንስቶ የትኛውንም አህጉር እና ዓለም አቀፍ ውድድሮችን በሜዳው እንዳያስተናግድ መታገዱ ይታወቃል።ቡድኑ ጨዋታዎችን ከሚያደርግባቸው ስታዲየሞች መካከል አንዱ የሆነው የባሕርዳር ስታዲየምም ይኸው ዕጣ ደርሶት ከዓለም አቀፍ ውድድሮች ርቆ ቆይቷል።በቅርቡ ግን የአማራ ክልል መንግሥት ስታዲየሙ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ በተቻለ ፍጥነት ይጠናቀቅ ዘንድ ተጨማሪ በጀት በማፅደቅ የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ጀምሯል። ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በባለሙያዎቹ አማካይነት በተለያዩ ጊዜያት ምልከታዎችን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን፤ ሂደቱ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝም ይፋ አድርጓል።

ከፕሮጀክቱ ባለቤት የአማራ ክልል ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ፤ እንዲሁም፣ ከተቋራጮች ጋር በመሆን በስፍራው ተገኝተው ምልከታውን ያደረጉት በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የክለብ ፈቃድ አሰጣጥ መምሪያ ኃላፊ አቶ አምሐ ተስፋዬ ሲሆኑ፤ ስታዲየሙ የካፍ መመዘኛን በጠበቀ መልኩ ግንባታው እየተከናወነ መሆኑን፣ በተለያዩ ምዕራፎች ተከፍሎ እየተከናወነ እንደሚገኝ፤ የማሻሻያ ሥራውም በመጫወቻ ሜዳ፣ በልምምድ ሜዳ፣ በስታዲየም ዙሪያ፣ በተለያዩ ክፍሎች እና የመስመር ዝርጋታዎች ላይ ያተኮረ እንደ ሆነ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የብሔራዊ ቡድን ጨዋታዎችን በሜዳዋ እንዳታደርግ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ክልከላው እንዲደረግባት ካደረጉ ጉዳዮች መካከል ዋንኛው የመጫወቻ ሜዳን የሚመለከት መሆኑ ይታወቃል።በዚህም በሃገር ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ ሜዳ መገንባት የሚችል ድርጅት ባለመኖሩ በውጪ



የባሕርዳር ስታዲየም የመጫወቻ ሜዳና የፍሳሽ መስመር በአዲስ መልክ በመገንባት ላይ ይገኛል፤

ሃገራት ባለሙያዎች እንድታሠራም ግብረ መልስ ተሰጥቶ የነበረ መሆኑ ይታወሳል።በመሆኑም የባሕርዳር ስታዲየም ሜዳ የፊፋ እና ካፍ ፍቃድ ባለው የፈረንሳይ ድርጅት ግሪጎሪ ኢንተርናሽናል እየተከናወነ መሆኑን ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

ግንባታው ከዚህ በፊት የነበረውን ሜዳ ሙሉ ለሙሉ ያነሳ ሲሆን፤ በዚህ ወቅትም የፍሳሽ መስመሮች ዝርጋታ እየተሠራ ይገኛል። በተጓዳኝም የአፈር እና አሸዋ ምርመራ ተጠናቆ ዝግጁ በመሆኑ የመስመር ዝርጋታው እንደተጠናቀቀ የሚሞላ ይሆናል። ቀጣዩ ሥራ ሜዳውን በሣር መሸፈን ሲሆን፣ የሣር ዘር ከውጪ ለማስገባት በሂደት ላይ ነው። ዘሩ የኢትዮጵያን መመዘኛዎች ሟሟላቱ በግብርና ሚኒስቴር ካረጋገጠ በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ ይገባል።እንደተረጋገጠም፣ እጅግ ከፍተኛ የሚባል ሙቀት እና ከፍተኛ ቅዝቃዜ ያለውን የአየር ሁኔታ መቋቋም የሚችል የሣር ዝርያ በሦስት ወራት ውስጥ ዝግጁ ይሆናል። የሜዳውን ግንባታ በማከናወን ላይ የሚገኘው ተቋም የአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጇ አይቮሪኮስትን ጨምሮ በካሜሩን፣ ሞሮኮ፣ ቱኒዚያ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ሴኔጋልን በመሳሰሉ ሀገራት መሰል ፕሮጀክቶችን እየሠራ ይገኛል።በመሆኑም በውሉ መሠረት ደረጃውን የጠበቀ ሜዳ ሠርቶ እንደሚያስረክብ አረጋግጧል።

ከዋናው የመጫወቻ ሜዳው በተጨማሪም ግንባታው ሁለት የልምምድ ሜዳዎችን ሲያካትት፤ በግሪጎሪ አማካኝነት ከመጫወቻ ሜዳው ጋር በተመሳሳይ የጥራት ደረጃ የሚከናወን ይሆናል። የሁለቱም የልምምድ ሜዳዎች የመታጠቢያ እና የልብስ መቀየሪያ ክፍሎች ተሠርተው የተጠናቀቁ ሲሆን፤ የፓውዛ ተከላ ተጀምሯል። አጥሮች እና መጠነኛ ተመልካች የሚይዝ የብረት የተመልካች መቀመጫም እየተሠራለት ይገኛል። ከሜዳዎቹ ሥራ ባለፈ ወደ ስታዲየሙ የሚያስገቡ በሮች ከሁለት ወደ አምስት እንዲያድጉ ተደርጓል። ተመልካቾችና ሌሎች ባለሙያዎች ከውጪ ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ ወደ ቪአይፒ፣ ቪቪአይፒ፣ ሚዲያ እና የእግር ኳስ ቡድኖች መኪና ማቆሚያ መግቢያዎች እየተሠራ የሚገኝ ሲሆን፤ የደጋፊዎች መኪና ማቆሚያ እና እግረኛ መግቢያም ተለይቶ ሥራዎች ተጀምረዋል።

በስታዲየሙ ከዚህ ቀደም በካፍ አስተያየት የተሰጠባቸው አስፈላጊ ክፍሎች ግንባታቸው እየተከናወነ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም የነበሩትንም ደረጃቸውን የማሳደግ ሥራ በመከናወን ላይ ነው። ስታዲየሙ በአንድ ጊዜ አራት ቡድኖችን ለማስተናገድ በሚያስችል መልኩ አራት መልበሻ ክፍሎች እና የዳኞች መልበሻ ክፍል ግንባታ እየተደረገለት ይገኛል። በቀጣይም የሊፍትና የተመልካች ወንበር ገጠማ፣ የስክሪን ገጠማ፤ እንዲሁም በምሽት ጨዋታ ለማድረግ የሚረዳ ፓውዛ ለመግጠም ዝግጅት ተጀምሯል።

ስታዲየሙ የማሻሻያ ግንባታውን ሙሉ ለሙሉ ሲያጠናቅቅም በካፍ መመዘኛ አራተኛ ላይ (የካፍ የመጨረሻ የጥራት ደረጃ መመዘኛን የሚያሟላ) ሆኖ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ማለት የብሔራዊ ቡድን ጨዋታዎችን (የአፍሪካ ዋንጫን ጨምሮ) እስከ ፍጻሜ ድረስ፤ እንዲሁም፣ የአፍሪካ የክለብ ውድድሮችን የማስተናገድ አቅም ይኖረዋል።የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንም በየጊዜው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር እና የመስክ ጉብኝት በማድረግ ክትትል እና ሙያዊ ድጋፍ ከማድረግ ባለፈ የውጪ ሀገራት ተሞክሮ እንዲወሰድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ይገኛል።

## ኦሮሚያ ክልል

ንብረትነቱ የአቶ ተክላይ አብርሃ የሆነ የመኪናው ዓይነት ዳማስ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-762079 የሻንሲ ቁጥር DA524-202896 ሞዴል DAJ2V ሞተር ቁጥር F6A-7139382 ሊብሬ ጠፍቶብኛል በማለት አሳውቀውናል፡፡ ስለዚህ የጠፋውን እቃ (ሊብሬ) ወድቆ ያገኘ ወይም ለሌላ ምክንያት ተይዟል የሚል ሰው ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 (አስራ አምስት) ቀን ጊዜ ውስጥ ለጽ/ቤታችን ሪፖርት ካላደረገ ለባለንብረቱ ሌላ ምትክ ሊብሬ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የፉሪ ክፍለ ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 01- A05280 ኦሮ የሆነ ሰሌዳ ጠፍቶብኛል ብለው አቶ ኢስጥፋኖስ ኡስማነ በቀን 11/04/16 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሰሌዳን በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ ካላቀረበ መ/ቤቱ ለባለንብረቱ ሌላ ተለዋጭ ሰሌዳ የሚሰጥ መሆኑን ያስታውቃል፡፡

**የምዕራብ አርሲ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን**

የባለንብረቱ ስም ሙሉሰው አያሌው የተሽከርካሪ ዓይነት ባጃጅ ሰሌዳ ቁጥር 1-32669 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር MD2A25BZXZKWE16650 የሞተር ቁጥር AZZDKt36335 ከላይ የተገለፀው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው አመልክተዋል፡፡ይህንን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያድጉ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የቡራዩ ክፍለ ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## ድሬዳዋ አስተዳደር

የባለንብረቱ ስም አህመድ በሽር ኡስማን ሰሌዳ ቁጥር 3-04735 ድሬ የተሽከርካራ ዓይነት ድርብ ተግባር የሻንሲው ቁጥር፡JTFBV71J9H7650353 ሞዴል VDJ79L-DKMRYV የሞተር ቁጥር ፡1VD-0384850 ሰሌዳ ቁጥር 3-04735 ድሬ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሰሌዳ የፊት የኋላ ጠፋብኝ ብለው በ8/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ባለስልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ተፈራ አሰፋ ጫካ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B19175 የተሸከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር KSP90-2090061 ሞዴል DBA-KSP90-AHXNK የሞተር ቁጥር 1KR-0911885 የሊብሬ ቁጥር 601679/579938 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪው ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ17/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

በአመልካች ወ/ሮ ሳምራዊት በለጠ /ሞግዚት አስተዳደሪ እና በተጠሪ ወ/ሮ መርሀዊት ጋሻው በተጠሪ አድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ስላልቻሉ ለ13/05/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች/የፍ/ባለመብት ስኬት ባንክ አ/ማ እና በተከሣሾች/ተጠሪዎች የፍ/ባለዕዳዎች 1ኛ ገነት ሀሰን፣ 2ኛ ጽጌ ተክሉ፣ 3ኛ ሙሉ ገ/ኪዳን፣ 4ኛ አስናቀች ወ/ትንሳዬ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባን/ኢን ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ23/05/2016 ዓ.ም. በ9፡50 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡና ክስ ለመስማት ለ28/05/2016 ዓ.ም. በ9፡20 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በአመልካች አቶ አማረ አስማማው አዲሱ እና በተጠሪ 1ኛ ሰለሞን በቀለ ሰንበታ 2ኛ መሳይ ግርማ ሰጉ ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 13/05/2016 ዓ.ም ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 9ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**